በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ
የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ዩኒቨርሲቲው የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታጁ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል::

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበ□ል::

- □□ቢ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

<u>**ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣**</u>

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ለተለያዩ ዕቃዎች ግዢ ከተከፈለው ክፍያ ላይ ብር 7,704.00 የቅድሚያ የገቢ ግብር ተቀናሽ ሳይደረግ ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ መንግስት ማግኘት የሚገባውን የታክስ ገቢ በወቅቱ እንዳያገኝ አድርጎታል::
2. ለቢሮና ለእንግዳ ማረፊያ አገልግሎት ለሚሆኑ ቤቶች ኪራይ ክፍያ ሲፈጸም አገልግሎት አቅራቢዎቹ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ከክፍያቸው ላይ 30% የቅድመ ግብር ክፍያ ተቀናሽ መደረግ ሲገባው 2% ብቻ በመቀነሱ ብር 361,520.00 ያልተሰበሰበ ገቢ መሆኑ፤
3. በተለያዩ የኮሚቴ ሥራዎች ለተሳተፉ፤ የተማሪዎች ምረቃ ላስተባበሩ እና የተማሪዎችን መረጃ በኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓት (SIMS) ላስገቡ፤ ለተቆጣጠሩና ሥራውን ላስተባበሩ በሚል በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ውሳኔ ብር 800,240.00 ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ፤

4. በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚገኙ የአስተዳደር ሰራተኞች ከመደበኛ የሥራ ቦታቸዉ ወደ ሌላ ሥራ ቦታ ሳይሄዱ ቅዳሜና እሁድ በዩኒቨርሲቲዉ ትርፍ ሰዓት ለሰሩበት በሚል ብር 817,244.40 አላግባብ የዉሎ አበል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
5. በቀን 05/13/2012 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 194512 በሂሳብ መደብ 6253 ለማታ እና ለቅዳሜና እሁድ (week-end) ትምህርት መርሀ-ግብር ማስታወቂያ የተከፈለው ብር 120,060.00 ከውስጥ ገቢ መከፈል ሲገባው ከመደበኛ በጀት የተከፈለ በመሆኑ አለአግባብ የመደበኛ ወጪ ከፍ እንዲል አድርጎታል፤
6. ዩኒቨርሲቲው ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጫ ማዕከል (ቁጥር 3) ጋር ለመምህራን የጋራ መኖሪያ ቤት የሚውል የ30/90 አምፔር የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ውል ገብቶ በመጠቀም ላይ የሚገኝ ሲሆን የኤሌክትሪክ ተቋሙ ባደረገው የመስክ ምልከታ ነዋሪዎች ከቆጣሪ ውጭ በስርቆት የተጠቀሙበት 79 ኪሎ ዋት የኤሌክትሪክ ክፍያ ብር 1,661,553.71 በቀን 17/3/2013 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 194947 በሂሳብ መደብ 6257 በዩኒቨርሲቲው ማኔጅመት ውሳኔ ከመደበኛ በጀት የተከፈለ በመሆኑ አለአግባብ የግለሰቦችን እዳ ዩኒቨርስቲው እንዲከፍል ተደርጓል፤
7. ዩኒቨርሲቲው የዕቃ ግዢ ለመፈጸም ከተለያዩ አቅራቢዎች ጋር በገባው የግዢ ስምምነት መሠረት አቅራቢዎቹ ከውል ስምምነቱ ውጭ ላዘገዩበት የጉዳት ካሳ ብር 583,526.62 ከአቅራቢዎች የግዢ ክፍያ ላይ መቀነስ ሲኖርበት ያልተቀነሰ (ያልተሰበሰበ) መሆኑ፤
8. ዩኒቨርሲቲው የተሟላ የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሰራተኞች ያሉት ቢሆንም የዩኒቨርሲቲዉ መምህራን በዘርፉ ህጋዊ ፍቃድ የሌላቸዉ መሆኑ እየታወቀ የዩኒቨርሲቲዉን ግቢ የምድር ገፅ ጥናትና ዲዛይን ሥራ ለማሰራት ከመምህራን ጋር የብር 1,612,320.00 የሥራ ውል ስምምነት ገብቶ ሥራው እየተከናወነ የሚገኝ መሆኑ እና ከተገባዉ የዉል ስምምነት ዉስጥ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ በቀን 25/10/2013 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 193379 ብር 627,760.00 የተከፈለ መሆኑ፤
9. በቀን 10/09/2013 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 207617 በሂሳብ መደብ 6233 የአስር አመት እስትራቴጂክ እቅድ ላይ ለተሳተፉ 7 ሰራተኞች የመስተንግዶ አገልግሎት ለኦዳ ነቤ ሆቴል ብር 64,292.79 ተከፍሎ ሳለ ለእነዚህ 7 ሰራተኞች በቀን 30/06/2013 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 207229 በሂሳብ መደብ 6231 ብር 113,269.80 በድጋሚ የውሎ አበል ክፍያ አላግባብ የተፈጸመ መሆኑ እና እንዲሁም በቀን 10/09/2013 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 207618 በሂሳብ መደብ 6233

የአስር አመት እስትራቴጂክ እቅድ ላይ ለተሳተፉ 6 ሰራተኞች የመስተንግዶ አገልግሎት ለኦዳ ነቤ ሆቴል ብር 53,638.83 ተከፍሎ ሳለ ለእነዚህ 6 ሰራተኞች በቀን 24/07/2013 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 207250 በሂሳብ መደብ 6231 ብር 86,880.00 በድጋሚ የውሎ አበል ክፍያ አላግባብ የተፈጸመ መሆኑ፤ በድምሩ ብር **200,149.80** (113,269.80 + 86,880.00) በድጋሚ የውሎ አበል ክፍያ አላግባብ የተፈጸመ መሆኑ፤

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

1. <u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)</u>

1.1. ዘላቂነት ባላቸው የሥራ መደቦች ላይ ሰራተኞችን በቋሚነት ቀጥሮ ማሰራት ሲገባ በተማሪዎች ምግብ ቤት እና በጠቅላላ አገልግሎት ክፍል ሰራተኞች በጊዚያዊነት ተቀጥረው በቀን በብር 60.00 እና ከዚያ በላይ የክፍያ ተመን በድምሩ ብር 1,439,337.00 በበጀት ዓመቱ ለጊዚያዊ ሰራተኞች ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤

1.2. በድምሩ ብር 3,095,901.75 ትክክለኛ ባልሆነ የወጪ ሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤

1.3. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሳይፈቅድ በበጀት ዓመቱ ለተለያዩ ሰራተኞች **በዋናው ግቢ** ብር 418,287.16 እና **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** ብር 1,080,798.58 በድምሩ ብር 1,499,085.74 የትርፍ ሰዓት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

1.4. የግዢ ፍላጎትን በማሰባሰብ ግልፅ ጨረታ በማውጣት የተለያዩ ድርጅቶችን በማሳተፍ ግዢ መፈጸም ሲገባ **በዋናው ግቢ** የብር **3,661,503.79 ግዢ** በዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) የተፈጸመ መሆኑ፣

1.5. ዩኒቨርሲቲዉ በግዥ መለያ ቁጥር ድ/ዳ/ዩ/ግ/ጨ/19/2013 ለተማሪዎች ምግብ ቤት የሚዉል የከብት ስጋ ለመግዛት ባወጣው ጨረታ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ሳያዘጋጅና የአቅራቢዎች አቅም ሳይገመግም በዝቅተኛ ዋጋ ላይ ብቻ በተመሰረተ የዋጋ ግምገማ አሸናፊዉ እንዲለይ የተደረገ መሆኑ እና ለምለም አደራ የተባለዉ ተጫራች ስጋ በማቀነባበርና ማቅረብ (31111) የንግድ ስራ መስክ የንግድ ስራ ፈቃድ የሌለዉ በመሆኑ ከጨረታዉ ውድድር ውጭ መደረግ ሲኖርበት በጨረታዉ ተሳትፎ ዝቅተኛ ዋጋ በማቅረቡ የጨረታው አሸናፊ ተደርጎ ከዩኒቨርሲቲው ጋር የከብት ሥጋ አቅርቦት ግዢ ውል ገብቶ በበጀት ዓመቱ የብር **5,173,945.08** የከብት ስጋ ግዢ የተፈጸመ መሆኑ፤

1.6. ዩኒቨርሲቲው በጨረታ መለያ ቁጥር ድ/ዳ/ዩ/ዉ/ጨ/04/2013 በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ተጫራቾችን አወዳድሮ የጨረታው አሸናፊ ከሆነው ከትራይኖቫ ኃላ/የተ/የግ/ማኀበር የአንድ ላፕቶፕ ዋጋ በብር 119,025.00 ሂሳብ በቀን 29/07/2013 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 197289 በሂሳብ መደብ 6313 ብዛቱ 10 (አስር) HP Pavilion Gaming 7-CD ላፕቶፕ ኮምፒዩተር በብር 1,190,250.00 ግዢ የፈጸመ ሲሆን ግዢው የተከናወነው ወቅታዊ የገበያ ጥናት ሳይደረግ መሆኑ፤

1.7. በቀን 19/12/2012 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 194359 በለይቶ ማቆያ ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች የምግብ አገልግሎት ለሚውል የጤፍ ግዥ ለከፈለኝ የሺጥላ የእህል ንግድ ድርጅት ለተከፈለው ብር 215,000.00 ሕጋዊ የክፍያ ደረሰኝ መቅረብ ሲገባው በገቢዎች ሚኒስቴር እውቅና በሌለው ደረሰኝ (በተራ በፋክቱር) ሂሳቡ ተወራርዶ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

1.8. በድምሩ ብር 28,105,313.36 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤

1.9. ለዩኒቨርሲቲው በ2013 በጀት ዓመት የተመደበለት የተስተካከለ በጀት እና በሥራ ላይ የዋለው የወጪ ሂሣብ ሲነጻጸር በተለያዩ ሂሣብ መደቦች ከመደበኛ በጀት ብር 15,778,930.96 እና ከካፒታል በጀት ብር 221,507.50 በድምሩ ብር 16,000,438.46 ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት) መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2. <u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>

2.1. የዩኒቨርሲቲው የንብረት አመዘጋገብ፤ አያያዝ እና አጠባበቅ በፌደራል መንግስት ግዢና ንብረት አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 649/2001 መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

1. **<u>በቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤት (ዋናው ግቢ)፤</u>**
   - የቋሚ ዕቃ ንብረት ክፍል ሰራተኞች የራሳቸው ቢሮ የሌላቸውና በስቶር ውስጥ ስራቸውን የሚያከናውኑ መሆኑ፤
   - አዲስ U
   - PS ብዛት በቁጥር 70 ያለአገልግሎት ለረጅም ዓመት በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
   - በ2011 ዓ.ም ገቢ የተደረጉ ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚውሉ አዲስ ዊልቼር ብዛት በቁጥር 5 ያለአገልግሎት በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
   - በ2010 ዓ.ም ገቢ የሆኑ መቅረጫ በቁጥር 136፤ መቀስ በቁጥር 203፤ የወረቀት መብሻ በቁጥር 231፤ እስቴፕለር በቁጥር 67፤ እና የወረቀት መቁረጫ በቁጥር 10 ያለአገልግሎት በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
   - አዳዲስ ዕቃዎች እና የሚወገዱ ዕቃዎችና በአንድ ስቶር ተከማችተዉ የሚገኙ መሆናቸዉ፤
   - ለቋሚ ዕቃዎች ቢንካርድ የተዘጋጀላቸው ቢሆንም በሚፈለገበዉ ቦታ ያልተቀመጠ መሆኑ እና አቀማመጡ ካይዘንን ያለተከተለ መሆኑ፤
   - በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤
2. **<u>በአላቂ ዕቃዎች ግምጃ ቤት (ዋናው ግቢ)፤</u>**
   - የአላቂ ዕቃዎች ንብረት ክፍል ሰራተኞች የራሳቸው ቢሮ የሌላቸውና በስቶር ክፍል ውስጥ ስራቸውን የሚያከናውኑ መሆኑ፤
   - የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች፤ የደንብ ልብሶች እና የግንባታ እቃዎች በአላቂ ስቶር ተደባልቀው የተቀመጡ መሆኑ፤
   - በ2009 ዓ.ም ገቢ የሆኑ የውሃ ቧንቧ ዕቃዎች ዩኒየን ባለ 3 ኢንች ብዛት በቁጥር 130፤ ሪዲዩሰር ከ3 ወደ 1 ብዛት በቁጥር 290፤ ኢልቦው ብዛት በቁጥር 150 ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
   - በ2012 ዓ.ም ገቢ የተደረገ ኮላ ብዛት በቁጥር 680 ያለአገልግሎት በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
   - ለሻወር ቤት አገልፍግሎት የሚውሉ በርካታ ሽክላዎች ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
   - በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤

3. **በተመላሽ ዕቃዎች ግምጃ ቤት (ዋናው ግቢ)፤**

- አገልግሎት የማይሰጡ Pointer HP በቁጥር 36፤ Ponter Lexmark በቁጥር 9፤ Fax mashine በቁጥር 8፤ Printer በቁጥር 4፤ Desktop CRT/Moniter/ በቁጥር 66;LCD Moniter በቁጥር 50፤ Key bord በቁጥር 52፤ Prossesor በቁጥር 160፤ UPS በቁጥር 11፤ Lenovo laptop በቁጥር 10፤ Dell laptop በቁጥር 17፤ Toshiba laptop በቁጥር 66፤ HP Laptop በቁጥር 78፤ LCD Projection Epson በቁጥር 4፤ LCD sony በቁጥር 20፤ Scaner በቁጥር 6፤ OK printer በቁጥር 55፤ Photo copy በቁጥር 17፤ የሻይ ማፍያ በቁጥር 7፤ ማከፋፈያ በቁጥር 350፤ ፍሪጅ በቁጥር 3፤ የስልክ ቀፎ በቁጥር 31፤ ቴሌቪዥን 43 ኢንች በቁጥር 5፤ ቴሌቭዥን 32 ኢንች በቁጥር 1፤ ሳምሰንግ የእጅ ስልክ በቁጥር 4፤ ዴል ታብሌት በቁጥር 50 ፍሬ ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜ በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

2.2. የአስተዳደር ዘርፍ የሥራ መደቦች በሙሉ የሥራ ጊዜ የሚከናወኑ ሥራዎች እንደመሆናቸው ተገቢውን የሰው ሀይል በቅጥር፤ በዕድገት ወይም በዝውውር መመደብ ሲገባ በዩኒቨርስቲው የአካዳሚክ አስተዳደር ጉዳዮች ተ/ኃላፊ እና የለውጥና መልካም አስተዳደር ተ/ዳይሬክተር የአካዳሚክ ባለሙያዎች (መምህራን) ሆነው በተጠቀሱት የሥራ መደቦች ላይ በተደራቢነት በኃላፊነት እያገለገሉ የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

2.3. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በየበጀት ዓመቱ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ዩኒቨርሲቲው ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

የ2012 በጀት ዓመት ግኝቶች፤

- የአስተዳደር ሰራተኞች ከመደበኛ ስራቸው ውጭ በተማሪዎች ምረቃ ዝግጅት ስለተሳተፉ በሚል ሰራተኞቹ ለስራ ጉዳይ ከሚሰሩበት ቦታ ወደ ሌላ ባልሄዱበት ሁኔታ ብር 159,000.00 አላግባብ የውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሳይፈቅድ ለአስተዳደር ሰራተኞች በድምሩ ብር 1,035,023.40 የትርፍ ሰአት ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤
- ለትምህርት ውጭ ሃገር ለተላኩ መምህራን በየወሩ ግማሽ ደመወዝ መከፈል ሲገባዉ አላግባብ ብር 135,698.15 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤

- አገር ውስጥ ለሚማሩ መምህራን ድጋፍ ክፍያ መከፈል ከሚገባው በላይ ብር 8,400.00 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
- ለመምህራን በመመሪያው መሰረት ክፍያ መፈጸም ሲገባ ከተመን በላይ ጭማሪ በማድረግ በድምሩ ብር 139,440.00 አላግባብ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
- በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤

የ2011 በጀት ዓመት ግኝቶች፤

- የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዝዳንትና ም/ፕሬዝዳንቶችን በማስመረጥ ሂደት ውስጥ ለተሳተፉ ኮሚቴ አባላት ብር 91,800.00 እና ለ5 የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ብር 71,680.00 በድምሩ ብር 163,480.00 ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲውን ለለቀቁ ሰራተኛ (ወ/ሮ አፍሪካ ደጀኔ) ከመስከረም እስከ ሚያዚያ በድምሩ ብር 30,115.20 የደመወዝ ክፍያ አላግባብ የተከፈላቸው መሆኑ፤
- በዋና ግቢ ለተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ለተለያዩ አቅራቢዎች (ድርጅቶች) ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበው ብር 4,041,343.14 የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ፣

የ2010 በጀት ዓመት ግኝቶች፤

- ከእንግዳ መምህራን ክፍያ 30% (ሰላሣ በመቶ) የገቢ ግብር መቀነስ ሲገባው 2% (ሁለት በመቶ) ብቻ በመቀነሱ በዋናው ግቢ ብር 197,407.64 እና በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ብር 109,217.00 በድምሩ ብር 306,624.64 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
- በሲ.ኢ.ቢ. (CEB) ቤተ መፅሃፍት 5 የኮምፒዩተር RAM መጥፋታቸው ከክፍሉ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣
- ከተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር ለአስተዳደርና ልማት ም/ፕሬዚዳንት እና ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በተፃፈ ደብዳቤ በተማሪዎች መኝታ ቤት በነሐሴ 2009 ዓ.ም እና በመስከረም 2010 ዓ.ም ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ዕረፍት መሄዳቸውን እና የክረምት ተማሪዎች ትምህረት መጨረሳቸውን ተከትሎ 225 ፍራሾች እና ሁለት 32 ኢንች ቴሌቪዥኖች መጥፋታቸው የተገለጸ መሆኑ፣
- ከቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ እና ባለሙያዎች ጋር በጋራ የኦዲት ቡድኑ በንብረት አካላዊ እይታ ወቅት በብሎክ ቁጥር 22 ባለ ሦስት ፌዝ ከ200 ሜትር በላይ የሚረዝም ኬብል ተቆርጦ መጥፋቱ የተገለጸ መሆኑ፤
- ከምህንድስና ክፍል በቁጥር ድ/ዳ/ዩ/ምቡ/01013/2010 በቀን 26/2010 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ ማከሚያ ማዕከል ትልቅ SDB የብረት በሮች በቁጥር 45 እና የዊንግ ዶርሚተሪ 2

ህንጻ እድሳት ላይ እያሉ የተለያዩ የኤሌትሪክ ፊክስቸሮች (Breakers) መጥፋታቸው የተገለጸ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያሳሰብን ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

ጥር 2014

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፤

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁቱና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፤

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን ፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **የገቢ ሂሳብ፣**

1.1. **ከግዢ ክፍያ ላይ ያልተቀነስ (ያልተሰበሰበ) የቅድሚያ ግብር፤**

1.1.1. **ግኝት፣**

በገዢው ተይዞ ስለሚከፈል የቀደመ ታክስ ክፍያ አፈጻጸም ለማስተዳደር የካቲት 1995 የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ በአንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ቁጥር 1 በዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ ወቅት ገዥው ለሻጩ ክፍያ ሲፈጽም ከጠቅላላው ተከፋይ ሂሳብ 2% በማስቀረት ለግብር ባለስልጣን ገቢ ማድረግ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ስለመንግስት ገንዘብ ክፍያ አንቀጽ 14 የመደበኛና የካፒታል የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈፀሙ በተ.ቁ. 13 ከወጪው ወይም ከክፍያው ላይ ተገቢው የቅድሚያ የገቢ ግብር ተቀናሽ (withhold) መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ለተለያዩ ዕቃዎች ግዢ ከተከፈለው ክፍያ ላይ ብር 7,704.00 የቅድሚያ የገቢ ግብር ተቀናሽ ሳይደረግ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 1** ቀርቧል፡፡

1.1.2. **ስጋት፣**

በመመሪያ መሰረት ግብር የማይቀነስ ከሆነ መንግስት ከግብር ማግኘት የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

1.1.3. **የማሻሻያ ሃሳብ፣**

ሳይሰበሰብ የቀረው የቅድሚያ ገቢ ግብር ተሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ተቋሙ መመሪያና ደንቡን ተከትሎ ክፍያ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

1.1.4. **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

ያልተቀነሰውን ታክስ አጣርተን ማስተካከያ የምናደርግ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

1.2. ያልተሰበሰበ (ተቀናሽ ያልተደረገ) የገቢ ግብር፤

1.2.1. ግኝት፣

ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓም ጀምሮ ተግባራዊ በተደረገው የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና አዋጁን ለማስፈጸም ስለፌደራል የገቢ ግብር በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 410/2009 መሰረት፣1ኛ-ባለሙያዎች በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት አገልግሎት ለመስጠት የተቀጠሩ ከሆነ በአዋጁ አንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ቀጣሪው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለተቀጣሪው በሚከፍልበት ጊዜ ተቀጣሪው ከአንድ በላይ የሆነ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ እንዳለው ያወቀና ሌላው ቀጣሪ ውይም ሌሎቹ ቀጣሪዎች በጠቅላላው የተቀጣሪው ገቢ ላይ ተመስርተው የገቢ ግብሩን ቀንሰው እንደሚያስቀሩ ያወቀ እንደሆነ ቀጣሪው የተቀጣሪውን ገቢ በማጠቃለል ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር ቀንሶ ማስቀረት እንዳለበት፣ 2ኛ-የስራው አይነት ከቅጥር ጋር ግንኙነት የሌለው አገልግሎት ከሆነ በሀገር ውስጥ ከሚፈፀም ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት በአዋጁ አንቀጽ 92 በተቀመጠው ድንጋጌ እና አዋጁን ለማስፈጸም በውጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀጽ 63 መሰረት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የንግድ ስራ ፍቃድ ሲያቀርብ ከክፍያው ላይ 2% ቅድመ ግብር ተቀናሽ የሚደረግ ሲሆን አገልግሎት አቅራቢው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የንግድ ስራ ፍቃድ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 4 በተገለፀው መሰረት 30% ከጠቅላላው ክፍያ ላይ ተቀናሽ መደረግ ያለበት መሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ለቢሮና ለእንግዳ ማረፊያ አገልግሎት ለሚሆኑ ቤቶች ኪራይ ክፍያ ሲፈጸም አገልግሎት አቅራቢዎቹ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ከክፍያቸው ላይ 30% የቅድመ ግብር ክፍያ ተቀናሽ መደረግ ሲገባው 2% ብቻ በመቀነሱ ብር 361,520.00 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 2** ቀርቧል፡፡

1.2.2. ስጋት፣

በመመሪያ መሰረት ግብር የማይቀነስ ከሆነ መንግስት ከግብር ማግኘት የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

1.2.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

ከክፍያ ላይ ያልተቀነሰው (ያልተሰበሰበው) ግብር ተሰብስቦ ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ መደረግ ይኖርበታል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ከክፍያዎች ላይ በመመሪያው መሰረት ተቀናሽ መደረግ ያለባቸው የመንግስት ታክስና ግብር በአግባቡ እንዲሰበሰቡ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.2.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የቤት ኪራይ ክፍያ ሲፈፀም ባለቤቶቹ ባቀረቡት የግብር መለያ ቁጥር ዊዝሆልድ 2% ተቀንሶ የተከፈለ ሲሆን አከራይ ግለሰቦቹም በሚኖሩበት አካባቢ ለሚመለከተው ገቢዎች ባለስልጣን የአከራይ ተከራይ ግብር እየፈፀሙ መሆኑን ከሰነዶች ማረጋገጥ ችለናል፡፡ በተጨማሪም አሁን በተገለፀልን ማስተካከያ መሰረት ወደፊት ማንኛውንም ክፍያ ስንፈፅም የንግድ ፈቃድን መሰረት አድርገን ማስተናገድ እንዳለብን ከግኝቱ በመረዳታችን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የምናደርግ መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

2. <u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

2.1. <u>የጊዚያዊ ሰራተኞች ቅጥርን በተመለከተ፤</u>

2.1.1. <u>ግኝት፤</u>

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር መ80-839/1 በተፃፈ ደብዳቤ ዘላቂነት ባለው የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት (በጊዜያዊነት) በፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች ተቀጥረው ያልተቋረጠ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ሠራተኞች በቋሚነት እንዲመደቡ፣ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባልተመደበ እና ዘላቂነት በሌለው የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ መሰናበት እንዳለባቸው እና እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት /ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በመጀመሪያ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ዘላቂነት ባላቸው የሥራ መደቦች ላይ ሰራተኞችን በቋሚነት ቀጥሮ ማሰራት ሲገባ በተማሪዎች ምግብ ቤት እና በጠቅላላ አገልግሎት ክፍል ሰራተኞች በጊዚያዊነት ተቀጥረው በቀን በብር 60.00 እና ከዚያ በላይ የክፍያ ተመን በድምሩ ብር 1,439,337.00 በበጀት ዓመቱ ለጊዚያዊ ሰራተኞች ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 3** ቀርቧል፡፡

2.1.2. ሥጋት፤

አሰራሩ በመንግስት የበጀት አጠቃቀምና በዕቅድ አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ችግር ከማስከተሉም በተጨማሪ ዘላቂነት ባላቸው የስራ መደቦች ሰራተኞችን በጊዜያዊ ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት የሰው ሃይል በዕቅድ እንዳይመራና በመንግስት ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ሊያስከትል ይችላል፡፡

2.1.3. የማሻሻያ ሀሳብ፤

ዘላቂነት ባለው የስራ መደብ ላይ ሰራተኞችን በቀንና በኮንትራት/ጊዚያዊነት ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ የውስጥ ደረጃ እድገት ወይም የውጭ ቅጥር ማስታወቂያ በማውጣት ሰራተኞቹ በቋሚነት ሊመደቡ /ሊቀጠሩ/ይገባል፡፡ ለኮንትራት ሰራተኞች እየተከፈለ ያለው ክፍያም ሊቆም ይገባል፡፡ ለወደፊቱ እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር ለመፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄውን በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በማቅረብ ተቀባይነት ሲያገኝ ተፈጻሚ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በተቋሙ ውስጥ ያሉ የተለያዩ የስራ ክፍሎች በተለይም የተማሪዎች አገልግሎት እና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ስር በርካታ የጉልበት ሰራተኞችን የሚፈልግ በመሆኑ የቀን ሰራተኞችን በጊዚያዊነት በመቅጠር ያሰራናቸው ሲሆን ነገር ግን ከሰኔ 2013 ዓ.ም ጀምሮ የጉልበት ሰራተኞችን በቋሚነት በመቅጠር እያሰራናቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2.2. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሳይፈቅድ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፤

2.2.1. ግኝት፤

የገንዘብና ሚኒስቴር በቀን 17/09/2002 በቁጥር ገ/ኢ/ል/ሚ/1/54/2/ ስለ ትርፍ ሰዓት ክፍያ አፈጻጸም በማስመልከት በጻፈው ደብዳቤ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 የተላለፈዉ የአፈጻጸም መመሪያ ተግባራዊ ሳይደረግ የቆየ መሆኑን ጠቅሶ መመሪያው በሥራ ባህሪያቸዉ ምክንያት ከመደበኛ ሥራ ሰዓት ውጭ ጭምር ለሚሰሩ የመንግስት መ/ቤቶች ጠቃሚ እንደሚሆን ስለታመነበት ያለአግባብ ብክነት እንዳይከሰት የተጠቃሚ መ/ቤቶች የሥራ ሁኔታዎች ግምት ዉስጥ በማስገባት በኮሚሽኑ በኩል በልዩ ሁኔታ እየተፈቀደ ሥራ ላይ እንዲዉል አሳስቧል፡፡ በዚሁ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፤

- የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሳይፈቅድ በበጀት ዓመቱ ለተለያዩ ሰራተኞች **በዋናው ግቢ** ብር 418,287.16 እና **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** ብር 1,080,798.58 በድምሩ ብር 1,499,085.74 የትርፍ ሰዓት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 4** ቀርቧል፡፡

2.2.2. **<u>ሥጋት</u>**፤

ክፍያዎች በደንብና መመሪያ መሰረት የማይፈጸሙ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

2.2.3. **<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**፤

ክፍያዎች በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲፈጸሙ ማድረግ ይገባል፡፡ በሥራ ጫና ምክንያት የትርፍ ሰዓት ሥራ ማሰራት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጥያቄውን በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በማቅረብ ሲፈቀድ ብቻ ክፍያው እንዲፈጸም ማድረግ ይገባል፡፡

2.2.4. **<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>**፤

- **<u>የዋናው ግቢ ምላሽ</u>:-** በተቋሙ ውስጥ የተፈቀዱ መደቦች በበቂ ሁኔታ በሰው ሃይል የተሟሉ ባለመሆናቸው በርካታ ሰራተኞች ለትርፍ ስራ የተጋለጡ ሲሆን ክፍያቸውም የሚመለከተው አካል ፈቃድ መሰረት ተፈጻሚ ሲሆን ሰንብቷል፡፡ ነገር ግን አልፎ አልፎ ሲቪል ሰርቪስ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ዘግይቶ የሚፈቅድ በመሆኑና አንዳንዴም የተወሰኑ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ፍቃድ ጥያቄ ቀናቶችን ቆርጦ የሚልክ በመሆኑ ሰራተኛው የሰራበትን ነገር ግን የክፍያ ፍቃድ በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ሲቀር በማኔጅመት ውሳኔ ሲከፈል ቆይቷል፡፡ ይሁንና የ2014 ዓ.ም ከገባ ጀምሮ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ፍቃድ ሳያገኝ የሚከፈሉ የነበሩ የትርፍ ሰዓት ክፍያዎች ተቋሙ ሙሉ በሙሉ መክፈል ያቆመ መሆኑን እንገልጻለን፡፡
- **<u>የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ምላሽ</u>:-** ከከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ የከፍተኛ ትምህረት ተቋማት የፕሮግራም ኦዲት እንዲያደርጉ ባዘዘውና ለዚህም ማስፈፀሚያና በላከው መመሪያ ላይ በመተራንስ የሚመለከታቸው አካላት ስራው ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ ስራው ሰፊ በመሆኑ ከመደበኛው የስራ ሰዓት ውጪ በትርፍ ሰዓት ለሰሩ መምህራንና ሰራተኞች የተከፈለ ክፍያ ነው፡፡

2.3. ለማስተባበር ሥራ እና በኮሚቴ ሥራ ለተሳተፉ የተፈጸመ ክፍያ፤

2.3.1. ግኝት፤

የፌደራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግሥት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤቱ ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ላይ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በተለያዩ የኮሚቴ ሥራዎች ለተሳተፉ፤ የተማሪዎች ምረቃ ላስተባበሩ እና የተማሪዎችን መረጃ በኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓት (SIMS) ላስገቡ፤ ለተቆጣጠሩና ሥራውን ላስተባበሩ በሚል በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ውሳኔ ብር 800,240.00 ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 5** ቀርቧል፡፡

2.3.2. ስጋት፤

ክፍያዎች በደንብና መመሪያ መሰረት የማይፈጸሙ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

2.3.3. የማሻሻያ ሀሳብ፤

ክፍያው በመመሪያ ያልተደገፈ በመሆኑ ተመሳሳይ ክፍያ እንዳይፈጸም የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ዩኒቨርሲቲው የመንግስት ደንብና መመሪያዎችን ጠብቆ ሥራውን ማከናወን ይኖርበታል፡፡

2.3.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

- በተለያዩ ኮሚቴዎች ተሳትፎ ለነበራቸው ግለሰቦች የተከፈሉት ክፍያዎች ከአሁን በፊትም ሲፈፀም የነበረ የሙያ ክፍያ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- SIMS የተማሪዎች መረጃ በአጠቃላይ ለማስተዳደር ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ እንስቲትዩት ሶፍትዌር መግዛቱን ይታወቃል፡፡ ሲስተሙ አዲስ ከመሆኑ ጋር አጠቃላይ የተማሪዎች መረጃ በመደበኛ ስራ ለመጨረስ የማይቻል መሆኑን የዩኒቨርሰቲው ማኔጅመንት ካረጋገጠ በኋላ አምስት ቴክኒካል ኮሚቴ በማደራጀት የፕሮጀክት አክሽን ፕላን እንዲዘጋጅ አቅጣጫ አስቀምጦ ስለሆነም ቴክኒካል ኮሚቴ ያዘጋጀውን ፕሮፖዛል በዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ካጸደቀ በኋላ እያንዳንዱን

የተማሪዎች መረጃ የሚያቀርቡ ባዮግራፊና ግሬድ የሚያስገቡ የገባውን መረጃ ትክክለኛነቱን የሚያረጋግጡ ሰራተኞች ጋር ውል በመግባባት እያንዳንዱን ክፍያ ማኔጅመንት ባጸደቀው መሰረት እንዲከፈል ተደርጓል፡፡

2.4. ከመመሪያ ውጭ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ፤

2.4.1. ግኝት፤

የካቲት 2012 ዓ.ም የወጣው የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2012 በክፍል 3 አንቀጽ 9 ከተራ ቁጥር 1-4 "ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ ወደ ሌላ ሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ከመላኩ በፊት የቀን ውሎ አበል መጠየቂያ፤ መክፈያና መፍቀጃ ቅጾች ለጉዳዩ አግባብ ባለው ሠራተኛ ወይም የሥራ ኃላፊ እንዲሞሉ ይደረጋል፡፡ የቀን ውሎ አበል እንዲከፈል የጠየቀ የሥራ ኃላፊ በሠራተኛ የተሞላ ቅጽ በትክክል መሞላቱን ያረጋግጣል፡፡ የቀን ውሎ አበል እየተከፈለው ወደ ሌላ የሥራ ቦታ የተላከ የመንግስት ሰራተኛ ሥራውን አጠናቆ ሲመለስ የቀን ውሎ አበል መቆጣጠሪያና የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ በመሙላት ስላከናወናቸው ሥራዎች መግለጫ እንዲያቀርብ ይደረጋል" በማለት ይገልጻል፡፡ የውሎ አበል ክፍያ በዚሁ መሠረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚገኙ የአስተዳደር ሰራተኞች ከመደበኛ የሥራ ቦታቸዉ ወደ ሌላ ሥራ ቦታ ሳይሄዱ ቅዳሜና እሁድ በዩኒቨርሲቲዉ ትርፍ ሰዓት ለሰሩበት በሚል ብር 817,244.40 አላግባብ የዉሎ አበል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 6** ቀርቧል፡፡

2.4.2. ሥጋት፤

ከመመሪያ ውጭ ክፍያ መፈጸም የመንግስት ዉስን ሀብት አላግባብ እንዲባክን ያደርጋል፡፡

2.4.3. የማሻሻያ ሃሳብ፤

የቀን ውሎ አበል ክፍያ የሚፈጸመው ሠራተኛው ከመደበኛ የሥራ ቦታው ወደ ሌላ ሥራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሲላክ በመሆኑ አላግባብ የተፈጸመው ክፍያ ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ተማላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ክፍያዎች በመንግስት መመሪያ መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፡፡

2.4.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ዩኒቨርሲቲያችን በቀን ለ24 ሰዓት በሳምንት 7 ቀን አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም በመሆኑ እና ተቋሙም ካለበት የሰው ሀይል እጥረት አብዛኛውን የስራ መደቦችን ሰራተኞችን ደርቦ በማሰራ እና የዕረፍት ጊዜያቸውን ጭምር በማሰራት ተጨማሪ አገልግሎት የሰጡበት ክፍያ የተፈፀመላቸው ሲሆን በኦዲቱ በተሰጠን አስተያየት መሰረት ከሐምሌ 1 ቀን 2013 ዓ/ም ጀምሮ ተመሳሳይ ክፍያ እንዳይፈፀም መመሪያ የተላለፈ እና የተቋረጠ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

2.5. ከመምህራን ጋር ውል ተገብቶ ለተሰራ የምድር ገፅ ጥናት ሥራ የተከፈለ ክፍያ፤

2.5.1. ግኝት፤

የፌደራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግሥት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤት ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ላይ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ዩኒቨርሲቲው የተሟላ የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሰራተኞች ያሉት ቢሆንም የዩኒቨርሲቲዉ መምህራን በዘርፉ ህጋዊ ፍቃድ የሌላቸዉ መሆኑ እየታወቀ የዩኒቨርሲቲዉን ግቢ የምድር ገፅ ጥናትና ዲዛይን ሥራ ለማሰራት ከመምህራን ጋር በቀን 14/04/2013 የብር 1,612,320.00 የሥራ ውል ስምምነት ገብቶ ሥራው እየተከናወነ የሚገኝ መሆኑ፤
- ከተገባዉ የዉል ስምምነት ዉስጥ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ በቀን 25/10/2013 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 193379 ብር 627,760.00 የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2.5.2. ስጋት፤

- ከመመሪያ ውጭ ግልጽነት የጎደለው የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን ያደርጋል፡፡
- ዉል የተገባዉ ከተቀጣሪ መምህራን ጋር በመሆኑና ህጋዊ የሥራ ፈቃድ የሌላቸዉ በመሆኑ ሊፈጠር ለሚችል የስራ ግድፈት ኃላፊነት የሚወስድ አካል እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

2.5.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ከመምህራን ጋር ውል ገብቶ ሥራው እንዲከናወን ማደረጉ ተገቢ ባለመሆኑ በግዢ መመሪያ መሠረት ሕጋዊ የሥራ ፈቃድ ያላቸው ድርጅቶችን በማወዳደር ሥራው ሊሰራ ይገባል፡፡

2.5.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ዩኒቨርሲቲያችን የግቢውን ምድረ ገፅ /ላንድስኬፕ/ በዘላቂነት ለማሰርት በርካታ ጊዜ በአማካሪ ድርጅቶች ቢያስጠናም በድርጅቶቹ የቀረበው ዋጋ ከብር 7,000,000.00 /ሰባት ሚሊዮን/ በላይ በመሆኑ ይህም ገንዘብ በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ዩኒቨርሲቲያችን ባሉት ባለሞያዎችና መምህራን ስራውን ሲያስጠና የቀረበው የዋጋ ዝርዝር ብር 2,000,000.00 /ሁለት ሚሊዮን/ ገደማ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው በዝቅተኛ ወጪ እና በራስ አቅም ስራውን ማሰራት እንዳለበት በመወሰኑ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሞያዎች የጥናትና የዲዛይን ስራው መሰራቱን እየገለፅን በዩኒቨርሲቲያችን ያለው የፕሮጀክት ጽ/ቤት ይህንን ስራ ለመስራት የሚያስችል አደረጃጀትም ሆነ የባለሞያ ስብጥር የሌለው መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

2.6. ለኤሌክትሪክ አገልግሎት አላግባብ የተፈጸመ ክፍያ፤

2.6.1. ግኝት፣

የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649 አንቀፅ 8 የመንግስት መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ኃላፊነት የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ስለሚያከናዉኑት ግዥና ስለሚያስተዳድሩት ንብረት ጠቅላላ ኃላፊነት ያለባቸዉ መሆኑን፤ እንዲሁም የመንግስት ግዥ በመስሪያ ቤቱ እቅድና ፍላጎት ላይ ተመስርቶ እንዲፈፀምና የመንግስት ንብረት ኦኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ እንዳለባቸዉ ያዛል፡፡ የፌደራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 በክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች አንቀጽ 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤቱ ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ላይ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል:: የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤ -

- ዩኒቨርሲቲው ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጫ ማዕከል (ቁጥር 3) ጋር ለመምህራን የጋራ መኖሪያ ቤት የሚውል የ30/90 አምፔር

የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ውል ገብቶ በመጠቀም ላይ የሚገኝ ሲሆን የኤሌክትሪክ ተቋሙ ባደረገው የመስክ ምልከታ ነዋሪዎች ከቆጣሪ ውጭ በስርቆት የተጠቀሙበት 79 ኪሎ ዋት የኤሌክትሪክ ክፍያ ብር 1,661,553.71 በቀን 17/3/2013 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 194947 በሂሳብ መደብ 6257 በዩኒቨርሲቲው ማኔጅመት ውሳኔ ከመደበኛ በጀት የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2.6.2. ሥጋት፣

የአገልግሎት ክፍያዎች ላይ ወቅታዊ ቁጥጥር የማይደረግ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን ያደርጋል፡፡

2.6.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

የዩኒቨርሲቲዉ አስተዳደር ድርጊቱን በማጣራት ስርቆት የፈፀሙ ሰራተኞችን ለህግ በማቅረብ አላግባብ ከመንግስት ካዝና የተከፈለዉን ገንዘብ እንዲተኩ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

2.6.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በወቅቱ በመምህራን መኖሪያ ቤት በኃይል መቆራረጥ ምክንያት በተደጋጋሚ የቆጣሪ መፈንዳት በሚከሰትበት ወቅት በወቅቱ የነበረ ነዋሪ ለከፍተኛ እንግልት በመዳረጉ ለችግሩ መፍትሄ ለማግኘት በተደጋገሚ ለሚመለከተዉ አካል የኒቨርሲቲዉ አሳዉቆ መፍትሄ እንዲሰጠዉ የጠየቀ ቢሆንም ምንም አይነት ምላሽ ባለማግኘቱ የተነሳ የተቋሙ ኤሌክትሪክ ሰራተኞች የመኖሪያ ቤቶቹ ከቆጣሪ ዉጪ ሃይል እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ችግሩ ሳዩፈታ እስከ 2013 ዓ.ም የቆየ ሲሆን ከዛ በኋላ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ምስራቅ ሪጅን ፅ/ቤት ክፍተቱን ያገኘዉና ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ነዋሪዉ ያለቆጣሪ ሲጠቀምበት የነበረዉን የሃይል ፍጆታ ተሰልቶ ብር 1,7453,335.86 ዩኒቨርሲቲዉ መክፈል እንዳለበት አሳዉቆ ይህ የማይሆን ከሆነ ጉዳዩን ወደ ህግ እንደሚወስደዉ በማስጠንቀቁ፤ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ በመኖሪ ቤቶቹ ሲኖሩ የነበሩ መምህራኖች በመቀያየራቸዉ ምክንያት ክፍያዉን መምህራኖች እንዲከፍሉት ለማድረግ አዳጋች ሆኗል፡፡ በዚህ ምክንያት ዪኒቨርሲቲዉ በወቅቱ የተጠየቀዉን ገንዘብ ሊከፍል ችሏል፡፡

2.7. ከውስጥ ገቢ መክፈል ሲኖርበት አላግባብ ከመደበኛ በጀት የተፈጸመ ክፍያ፤

2.7.1. ግኝት፤

በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 የመንግስት ሂሳብ አያያዝ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 4 የመንግስት መ/ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ስርዓት መሰረት የተፈቀደላቸውን በጀትና የወጣውን ወጪ ማሳየት እንዲችሉ ተለይቶ በተሰጡዋቸው የበጀት መለያ መደቦች ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 በአንቀፅ 5 ንኡስ አንቀፅ 2 የውስጥ ገቢ ማስገኛ ስራዎች ወጪ በውስጥ ገቢ መሸፈን እንዳለበት ይገልፃል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በቀን 05/13/2012 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 194512 በሂሳብ መደብ 6253 ለማታ እና ለቅዳሜና እሁድ (week-end) ትምህርት መርሀ-ግብር ማስታወቂያ የተከፈለው ብር 120,060.00 ከውስጥ ገቢ መከፈል ሲገባው ከመደበኛ በጀት የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2.7.2. ሥጋት፤

ለመደበኛ ስራዎች የተፈቀደን በጀት ለሌላ ፕሮግራም ማዋል ከመመሪያ ውጭ ከመሆኑም በላይ ሥራዎች በዕቅድ እንዳይመሩ ያደርጋል፡፡

2.7.3. የማሻሻያ ሀሳብ፤

ዩኒቨርሲቲው የመንግሥት ደንብና መመሪያዎችን ጠብቆ ሥራውን ማከናወን ይኖርበታል፡፡ ለውስጥ ገቢ ስራዎች ማከናወኛ ከመደበኛ በጀት የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ ተደርጎ ለገንዘብ ሚኒስቴር ፈሰስ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.7.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የማስታወቂያ ክፍያ ሲፈፀም ሰራተኞች ላይ በነበረው የስራ ጫና ምክንያት የተፈጠረ ክፍተት ስለሆነ ማስተካከያ የምናደርግ መሆኑን እየገለፅን ለወደፊቱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የምናደርግ መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

2.8. ከዕቃ አቅራቢዎች ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሣ፤

2.8.1. ግኝት፤

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 (ሸ) አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ

ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቅቆ ባያስረክብ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደው እርምጃ በአቅራቢውና በመንግሥት መ/ቤት መካከል በሚደረግ ውል መካተት ይኖርበታል፤ እንዲሁም አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ላዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙ በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ መቀጣት እንዳለባቸው እና በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን 10% መብለጥ እንዳሌለበት ተገልጿል። በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ፤

- ዩኒቨርሲቲው የዕቃ ግዢ ለመፈጸም ከተለያዩ አቅራቢዎች ጋር በገባው የግዢ ስምምነት መሠረት አቅራቢዎቹ ከውል ስምምነቱ ውጭ ላዘገዩበት የጉዳት ካሳ ብር 583,526.62 ከአቅራቢዎች የግዢ ክፍያ ላይ መቀነስ ሲኖርበት ያልተቀነሰ (ያልተሰበሰበ) መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል። ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 7** ቀርቧል።

2.8.2. <u>ስጋት፤</u>

ዩኒቨርሲቲው የገዛቸው ዕቃዎች በውሉ መሠረት በወቅቱ ገቢ ካልሆኑ ለታለመለት ዓላማ ላይውሉ ይችላሉ።

2.8.3. **<u>የማሻሻያ ሃሳብ፤</u>**

ዩኒቨርሲቲው ኃላፊነታቸውን ከማይወጡ የዕቃ አቅራቢዎች ላይ የሚፈለገውን የጉዳት ካሳ በውሉ መሠረት ሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ ማድረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት የተገዙ ዕቃዎች በወቅቱ ቀርበው ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢውን ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል።

2.8.4. **<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>**

የተዘረዘሩትን ግዥዎች ሁሉንም ለማለት በሚያስችል ደረጃ የታዩት የማስገቢያ (የማስረከቢያ) ጊዜያት መዘግየት ከአቅራቢዎቹ ረገድ የተከሰተ ምክንያት ሳይሆን ዩኒቨርሲቲው የአቅርቦቱን እጥረት እና የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ መቅረቡን እንዲገመግመው የሚያቋቁማቸው ጊዜያዊ የቴክኒክ ኮሚቴ በአብዛኛው ሞያው ከሚመለከታቸው መምህራን ውስጥ ስለሆኑ በተለያዩ የማስተማርና ሌሎች ተግባሮች ስለሚያዙ በወቅቱ ተሟልተው ለመረከብ ባለመቻላቸው የተከሰተ ክስተት ነው። ስለሆነም አቅራቢዎቹ ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው ማመልከቻ ፅፈው ለፕሬዝዳንት ጽ/ቤት በማስገባት ወደ አስ/ተማ/አገ/ም/ትሬዝዳንት እንዲመራላቸው በማድረግ የውል

ማስከበሪያ ጊዜው እንዲራዘምላቸው ሲደረግ የቀየበት አግባብ ነው የነበረው እንጂ ጉድለቱ ከአቅራቢው ሆኖ ሲገኝ አንድም የጉዳት ካሳ ሳናስከፍል ዝም ብለን የምናልፈው አቅራቢ እንደሌለ እንዲታወቅ እያልን ለማስረጃነት በቅርቡ የ2013 ዓ.ም የሰራተኞችን የደንብ ልብስ የሰፋው አሀዱ የሚባል ድርጅት በራሱ ጥፋት የማስረከቢያ ጊዜው ስለዘገየ 1 ሚሊዮን ከማይደርስ ክፍያ ህጉ ባስቀመጠው አግባብ ከ77 ሺህ የሚበልጥ ብር በጉዳት ካሳነት እንዲቆረጥበት ተደርጎ ገቢ ሆኗል፡፡

2.9. <u>በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፤</u>

2.9.1. <u>ግኝት፣</u>

በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5 አንቀጽ 7 በተራ ቁጥር 4 መ/ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ስርአት መሰረት የተፈቀደላቸውን በጀትና የወጣውን ወጪ ማሳየት እንዲቻል ተለይቶ በተሰጣቸው የበጀት መለያ መደቦች ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በቀን 29/07/2013 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 197559 ለማህበረ ትጉሃን የእንጨት፤ ብረታብረትና ኮንስትራክሽን ሥራ ድርጅት ለሎከር ግዢ የተከፈለው ብር 2,965,901.75 በሂሳብ መደብ 6314 (ለዕቃዎች መግዣ) መመዝገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ በ6244 (ለዕቃዎች ዕድሳት) የተመዘገበ መሆኑ፤
- በቀን 11/03/2013 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 194939 ለመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የምክክር መድረክ ድጋፍ የተከፈለው ብር 130,000.00 በሂሳብ መደብ 6412 (ለተቋማት ድጋፍና ድጎማ) መመዝገብ ሲገባዉ በሂሳብ መደብ በ6256 (ለአገልግሎት ክፍያ) የተመዘገበ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 3,095,901.75 ትክክለኛ ባልሆነ የወጪ ሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2.9.2. <u>*ሥጋት፣*</u>

ወጪዎች በትክክለኛው የሂሳብ መደባቸው የማይያዙ ከሆነ የበጀት ዓመቱ የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታውን ካለማሳየቱም በተጨማሪ በበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

2.9.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው በጀት የሚመደብለት በየወጪ ሂሳብ ርዕሱ ተለይቶ ስለሆነ የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ክፍያ መፈፀሙ መመሪያን የጣሰ ከመሆኑም በላይ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ምክንያት ስለሚሆን ለወደፊቱ ሊስተካከል ይገባል፡፡

2.9.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በኦዲት ግኝቱ የተመለከትነው ስህተት ከሰነዱ ጭምር የተመለከትነው ሲሆን በባለሙያዎች የተፈጠረ ክፍተት በመሆኑ ለወደፊቱ የተሰጠንን ምክረ ሃሳብ ተግባራዊ የምናደርግ መሆኑን ለመገልፅ እንወዳለን፡፡

2.10. በዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) የተፈጸመ ግዢ፤

2.10.1. ግኝት፣

ሰኔ 2002 በወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀጽ 15/2 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተገለጸው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግሌጽ የጨረታ ዘዳ መፈጸም እንዳለባቸው፣ በአዋጁ አንቀጽ 33/4 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ አዋጁ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ሥርዓቶችን ለመሸሽ በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን የዕቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን በመከፋል እንደሌለባቸው እንዲሁም፣ በመመሪያው አንቀጽ 24/1 እና 24/4 መሠረት ሊታቀደ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋቸው በመመሪያው በተጠቀሰው መሠረት በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ዘዴ መፈፀም እንደሚቻል ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- የግዢ ፍላጎትን በማሰባሰብ ግልፅ ጨረታ በማውጣት የተለያዩ ድርጅቶችን በማሳተፍ ግዢ መፈጸም ሲገባ **በዋናው ግቢ** የብር **3,661,503.79 ግዢ** በዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) የተፈጸመ መሆኑ፣ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር** 8 ቀርቧል፡፡

2.10.2. ሥጋት፣

ግዥ በአዋጁና መመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባ፣ የአፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥት ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥም ይችላል፡፡

2.10.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በጥቅል ወይም በጅምላ ሊገዙ የሚችሉ እቃዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

2.10.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

1. በዝግጅት ምዕራፍ (በተማሪዎች ቅበላ) ወቅት በተለያየ የፀጥታ ችግርና ዩኒቫርስቲው የኮቪድ -19 ተጠርጣሪዎችን ለይቶ ማቆያ ሆኖ ሲያገለግል ከመቆየት አንፃር የጠሰባበሩ ቁልፎችን ለመተካት የተከናወነ ግዥ ሲሆን በግልፅ ጨረታ ረጅም ጊዜ ቆይቶ ይህን ግዢ ለመፋፀም የማይቻል በመሆኑን በግዢ መመሪያ አንቀጽ 24.1 እና 24.3 ላይ የተጠቀሱጥን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ የተከናወነ ግዢ መሆኑን ግንዛቤ ቢወሰድ እነላለን፡፡
2. በተራ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሱት የተከናወነ ግዥ ሲሆን ከሁለት ወር በኃላ በዘርፋ በአቀራቢነት ሰርትፊኬት የላቸው አቅራቢዎች ጥቂት ብቻ በመሆናቸው ከነዕርሱ ፕሮፎርማ በመሰብሰብ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ድርጅት አጋጣሚ ከላይኛው ጋር ተመሳሳይ ሆን እንጂ ሆን ተብሎ አንድን አካል ለመጥቀም የተደረገ እንዳልሆነ ግንዛቤ ቢያዝ እንላለን፡፡
3. በዚሁ በተማሪዎች ቅበላ የዝግጅት ምዕራፍ በተራ ቁጥር 1 እና 2 በተጠቀሰው ምክንያትና አላማ መመሪያውን ተከትሎ የተከናወነ ግዥ መሆኑን ግንዛቤ ቢወሰድ እንላለን፡፡
4. ከላይ ከተራ ቁጥር 1-3 ከተገለፁት ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ መመሪያውን ጠብቆ የተከናወነ ግዥ መሆኑን ግንዛቤ ቢያዝ እንላለን፡፡
5. ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያትና አላማ በተመሳሳይ ሁኔታ መመሪያውን ተከትሎ የተከናወነ ግዥ መሆኑን ግንዛቤ ቢያዝ እንላለን፡፡
6. ለተማሪዎች አገልግሎትና በአጠቃላይ ለዩኒቫርስቲው ማህበረሰብ የሚውል ከፍተኛ የውሃ እጥረት በማጋጠሙ በግቢው ውስጥ ተበላሽቶ የነበረውን የገድጎድ ውሃ የሚስብ ማሽን ለማስራት በአስቸኳይ ገዥው እንዲፈፀም ምክንያት መመሪያውን ተከትሎ የተከናወነ ግዥ መሆኑን ግንዛቤ ቢያዝ እንላለን፡፡
7. ይህ ግዥ ማዕቀፍ ላይ ያለ ቢሆንም በወቅቱ ተወዳድሮ ያሸነፈውን ድርጅት የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ስላላሳወቀን ለተማሪዎች የመመገቢያ እቃ ማጠቢያ በመጥፋቱ ከፍተኛ ችግር አጋጥሞን ስለነበር አስፈላጊነቱ

አንገብጋቢ ስለነበር መመሪያውን ተከትሎ የተከናወነ መሆኑን ግንዛቤ ቢያዝ እንላለን፡፡

8. በተራ ቁጥር 11 ላይ በተጠቀሰው መሰረት በተመሳሳይ ሁኔታ በጣም አስፈላጊ ግዥ በመሆኑ የተከናወነ ነው፡፡
9. የኤሌክትሪክ እቃዎችና የውሃ ማጠራቀሚያ ሮቶ በተማሪዎች መቀበያ የዝግጅት ምዕራፍ አስፈላጊነታቸው በጣም አንገብጋቢ እና ጊዜ የማይሰጥ መሆኑ ስለታመነበት መመሪያውን ተከትሎ የተከናወነ መሆኑን ግንዛቤ እንዲያዝ እንላለን፡፡

2.11. <u>የግዢ መመሪያን ያልተከተለ የሥጋ አቅርቦት ግዢ፤</u>

2.11.1. <u>ግኝት፤</u>

ሰኔ 2002 በወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀፅ 16.19.1.2.ሀ ማንኛዉም የመንግስት መ/ቤት በጨረታዉ የተወዳደረዉ አቅራቢ መ/ቤቱ የሚፈልገዉን አነስተኛዉን የጥራት መመዘኛና ሌሎች መሠረታዊ መስፈርቶች ያላሟላ በመሆኑ ብቃት የሌለዉ ሆኖ ሲገኝ ተጫራቹን ወደ ዝርዝር ግምገማ ማሳለፍ እንደሌለበት ይገልጻል፡፡ በፌዴራል የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ቁጥር አዋጅ 649/2001 አንቀፅ 29.2 የመንግስት መ/ቤቱ ሊገዛ የሚፈለገዉን ዕቃ ጥራት፤ ጠቀሜታ፤ ተገቢ ጥንቃቄ፤ እንደ አስፈላጊነቱ መለኪያዉን፤ መለያዉን፤ መጠሪያዉን፤ አስተሻሸጉን፤ ምልክቱን ወይም የአመራረት ሂደትና ዘዴ እንዲሁም ተፈላጊ የሆነዉን ባህርይ የሚያሟላ መሆኑ የሚረጋገጥበትን ሥርዐት የሚገልፅ መሆን እንዳለበት ያዛል፡፡ በ2002 የወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ በአንቀፅ 17.2.ለ የሚዘጋጀዉ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የዉሉ አንድ ክፍል በመሆን የአቅርቦቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚሁ መመሪያ አንቀፅ 5.2.2.3 ተጫራች ድርጅቶች ለስራዉ ብቁ መሆናቸዉን ለማረጋገጥ የአመልካቹን ቁልፍ ባለሙያዎች የሥራ ልምድ፤ የሚያስፈልግ ስራ የመፈፀም አቅም፤ ደረጃ፤ መሳሪያና ቁሳቁስ ያሟላ መሆኑ መገምገም እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በአንቀጽ 5.7.2 ለቴክኒክ ጥራት የሚሰጠዉ ክብደት ዝቅተኛ ወለል 70% መሆኑን ጠቅሶ በዚህ የመረጣ ስልት በቴክኒክ ግምገማ ከ70% በታች ያገኙ ተጫራቾች የቴክኒክ ሀሳብ ማቅረብያ ዉድቅ ይደረግና 70% እና ከዚያ በላይ ያገኙ ተጫራቾች የዋጋ መወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያ መከፈት እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚሁ መሰረት የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ዩኒቨርሲቲዉ በግዥ መለያ ቁጥር ድ/ዳ/ዩ/ግ/ጨ/19/2013 ለተማሪዎች ምግብ ቤት የሚዉል የከብት ስጋ ለመግዛት ባወጣው ጨረታ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ሳያዘጋጅና የአቅራቢዎች አቅም ሳይገመግም በዝቅተኛ ዋጋ ላይ ብቻ በተመሰረተ የዋጋ ግምገማ አሸናፊዉ እንዲለይ የተደረገ መሆኑ፤
- ለምለም አደራ የተባለዉ ተጫራች ስጋ በማቀነባበርና ማቅረብ (31111) የንግድ ስራ መስክ የንግድ ስራ ፈቃድ የሌለዉ በመሆኑ ከጨረታዉ ውድድር ውጭ መደረግ ሲኖርበት በጨረታዉ ተሳትፎ ዝቅተኛ ዋጋ በማቅረቡ የጨረታው አሸናፊ ተደርጎ ከዩኒቨርሲቲው ጋር የከብት ሥጋ አቅርቦት ግዢ ውል ገብቶ በበጀት ዓመቱ የብር 5,173,945.08 የከብት ስጋ ግዢ የተፈጸመ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ **በሰንጠረዡ** ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የባ/ወ/ማ/ቁ	የቀረበዉ እቃ አይነት	የገንዘብ መጠን
1	07/08/13	197299	ለተማሪዎች ም/ቤት የተፈጨ ስጋ አቅርቦት	1,791,248.73
2	17/09/13	197697	ለተማሪዎች ም/ቤት የተፈጨ ስጋ አቅርቦት	1,590,619.46
3	23/10/13	193372	ለተማሪዎች ም/ቤት የተፈጨ ስጋ አቅርቦት	1,792,076.89
			ድምር	**5,173,945.08**

2.11.2. ሥጋት፤

ግዥዎች በመንግስት የግዢ መመሪያ መሰረት የማይፈጸሙ ከሆነ ሕገወጥ አሰራርን ያስፋፋል፤ መስፈርቱን ያሟሉ ድርጅቶች እድል እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡ የመንግስት ውስን ሀብት ያለአግባብ እንዲባክን በር ሊከፍት ይችላል፡፡

2.11.3. የማሻሻያ ሀሳብ፤

ግዥዎች በመንግስት የግዢ መመሪያ መሰረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በየጊዜው ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በግኝቱ የተጠቀሰው ግዢ ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

2.11.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

- የንግድ ስራ ፈቃድን በተመለከተ ዘርፍ/31111/ የሚል ቢኖረውም በሌላ መልኩ 64118 የዘርፍ ቁጥር የምግብ አቅርቦቶች የሚል ስለሆነ ስጋም ከምግብ አቅርቦቶች አንዱ በመሆኑ በወቅቱ ይህ ግንዛቤ ተይዞ በውድድሩ እንዲቀጥል መደረጉ እና በፍፁም ቅን ልቡና የተሄደበት ሂደት መሆኑን እንገልፃለን፡፡

- የተጠቀሱትን የአቅርቦት ጥረት ቴክኒካል መስፈርቶችና ከዋጋ ባሻገር ሊታዩ የሚገቡ ሂደቶችን በተመለከተ በወቅቱ የተዘጋጀው ሰነድ ከዚህ በፊት ባሉ አመታቶች ሲዘጋጁ ከነበሩ የስጋ ግዥ የጨረታ ሰነዶች ጋር በተመሳሳይ መልኩ የተዘጋጀ እና መካተት የሚገባቸው መስፈርቶችም የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አዘጋጅቶ ወደታች የሚያወርዳቸውን ፎርማቶች የተከተለና እዚህ በግለሰብ ፍላጎት ሆን ተብሎ የሚቀነስ ወይም የሚጨመር ነገር እንዳልነበረ ቢታወቅልና በዚሁ አግባብ የተካሄደ ውድድር መሆኑን እየገለፅን ለዚሁ ማስረጃ ይሆን ዘንድ በ2012 እና ከዛ በፊት የተዘጋጁ የስጋ ግዥ ሰነዶችና የተፈረሙ ውሎችን አቅርቦ ማየት ቢቻል ጥሩ ነው ብለን እናምናለን፡፡
- በተጨማሪም ከዚህ በፊት በነበረው የስጋ አቅርቦት ላይ ብልሽት አጋጥሞ ተጠቃሚ ተማሪዎችና የተለያዩ የክፍሉ ሰራተኞች በተደጋጋሚ ቅሬታና ሮሮ ሲያሰሙ እንደቆዩ ማረጋገጥ የሚቻል ሲሆን ይህ አቅራቢ አሸንፎ ማቅረብ ከጀመረ በኋላ ግን ተጠቃሚዎቹ ተማሪዎች እርካታ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚገለፅና አንድም ቀን ቅሬታ ያልቀረበበት መሆኑን በየቀኑ በምንሰማው ግብረመልስ ማረጋገጥ የቻልን በመሆኑ የተነሱት ጉዳዮች በዚህ አግባብ ከዩኒቨርሲቲው አጠቃላይ የተጠቃሚነት መመዘኛ ቢታይ ጥሩ ነው የሚል እምነት አለን፡፡

2.12. <u>የዋጋ ጥናት ሳይደረግ በውስን ጨረታ የተፈጸመ የላፕቶፕ ኮምፒዩተር ግዢ፤</u>

2.12.1. <u>ግኝት</u>፣

በፌዴራል መንግስት የግዢ መመሪያ አንቀፅ 23.2.1.ለ. በጨረታዉ ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር በርካታ ቢሆንም፤ በአቅራቢዎች ዝርዝር ዉስጥ ከተመዘገቡት መካከል ፍትሐዊ በሆነ ምርጫ ቢያንስ አምስት ዕጩ ተወዳዳሪዎች በመመረጥ እና አቅራቢዎቹ ያቀረቡት ዋጋ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መሆኑን በጥናት በማረጋገጥ ግዢ መፈጸም እንደሚገባ ይገልጻል ፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ዩኒቨርሲቲው በጨረታ መለያ ቁጥር ድ/ዳ/ዩ/ዉ/ጨ/04/2013 በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ተጫራቾችን አወዳድሮ የጨረታው አሸናፊ ከሆነው ከትራይኖቫ ኃላ/የተ/የግ/ማኀበር የአንድ ላፕቶፕ ዋጋ በብር 119,025.00 ሂሳብ በቀን 29/07/2013 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 197289 በሂሳብ መደብ 6313 ብዛቱ 10 (አስር) HP Pavilion Gaming 7-CD ላፕቶፕ ኮምፒዩተር በብር 1,190,250.00 ግዢ የፈጸመ

ሲሆን ግዢው የተከናወነው ወቅታዊ የገበያ ጥናት ሳይደረግ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2.12.2. ሥጋት፣

የገበያ ዋጋ አለመጠናቱ ላፕቶፖቹ በተጋነነ ዋጋ ግዥ እንዲፈፀም የሚያደርግና የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ነዉ፡፡

2.12.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

ግዢዎች በግዢ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፡፡

2.12.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ዩኒቨርሲቲያችን 10 (አስር) HP Pavilion Gaming 7-CD ላፕቶፕ ኮምፒዩተር ግዥ ሲፈፅም እቃው ከሚያስፈልግበት ጊዜ አኳያ በጣም አጭር በመሆኑ የፌደራል መንግስት የግዥ መመሪያ ላይ ከተዘረዘሩት የግዥ አይነቶች ውስጥ ግዥውን ለመፈፀም ውስን ጨረታ ተመራጭ የግዝ ዘዴ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲያችን በውስን ጨረታ እንዲገዛ ውሳኔ በማስተላለፉ እና በዘርፉ አቅራቢ የሆኑ ድርጅቶችን በበቂ ሁኔታ በመጋበዝ ግዥው ሊፈፀም የቻለ መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን፡፡ በተጨማሪም ለወደፊቱ በኦዲቱ የተሰጠንን ምክረ ሀሳብ ተቀብለን ለመተግበር እንደምንጥር እየገለፅን የሚመለከታቸው ክፍሎችም ለተግባራዊነቱ እንዲንቀሳቀሱ መመሪያ የተሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

2.13. አላግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ክፍያ፤

2.13.1. ግኝት ፤

የፌደራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግሥት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤቱ ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ላይ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት**፡-

- በቀን 10/09/2013 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 207617 በሂሳብ መደብ 6233 የአስር አመት እስትራቴጂክ እቅድ ላይ ለተሳተፉ 7 ሰራተኞች የመስተንግዶ አገልግሎት ለኦዳ ነቤ ሆቴል ብር 64,292.79 ተከፍሎ ሳለ ለእነዚህ 7 ሰራተኞች

በቀን 30/06/2013 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 207229 በሂሳብ መደብ 6231 ብር 113,269.80 በድጋሚ የውሎ አበል ክፍያ አላግባብ የተፈጸመ መሆኑ፤

- በቀን 10/09/2013 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 207618 በሂሳብ መደብ 6233 የአስር አመት እስትራቴጂክ እቅድ ላይ ለተሳተፉ 6 ሰራተኞች የመስተንግዶ አገልግሎት ለኦዳ ነቤ ሆቴል ብር 53,638.83 ተከፍሎ ሳለ ለእነዚህ 6 ሰራተኞች በቀን 24/07/2013 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 207250 በሂሳብ መደብ 6231 ብር 86,880.00 በድጋሚ የውሎ አበል ክፍያ አላግባብ የተፈጸመ መሆኑ፤

በድምሩ ብር **200,149.80** (113,269.80 + 86,880.00) በድጋሚ የውሎ አበል ክፍያ አላግባብ የተፈጸመ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2.13.2. <u>ሥጋት፤</u>

ከመመሪያ ውጭ በድጋሚ ክፍያ መፈጸም የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን ያደርጋል፡፡

2.13.3. <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በዕቅድ ዝግጅት ላይ የተሳተፉ ሰራተኞች የምግብና የመኝታ ወጪ በሆቴል የመስተንግዶ አገልግሎት ተሸፍኖ ሳለ ለሰራተኞቹ የውሎ አበል ክፍያ መፈጸሙ አግባብ ባለመሆኑ የውሎ አበል ክፍያው ከሰራተኞቹ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.13.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

በኦዲት ማስራወሻው ላይ እንደተገለፀው ክፍያው የተከፈለው ከመንግስት በተቀመጠው አቅጣጫና ከዩንቨርስቲያችን ተቆርሶ በወረደልን መሰረት የአስር አመቱን እስትራቴጂክ እቅድ ወደ አዲስ አበባ ሄደው ሆቴል ተይዞላቸው ሲሰሩ ለቆዩ መምህራን ሲሆን፡-

- ➢ ስራውን ተረጋግቶ ለመስራት ከመደበኛው የስራ ቦታ እርቆ መስራት አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፤
- ➢ የሚሰራው እቅድ ብዙ መረጃዎች መሰብሰብና መተንተንን ስለሚጠይቅ ይህንን ለመስራት መረጃዎች የሚገኙበት ቦታ ድረስ ሄዶ መስራት የግድ በመሆኑ፤

ለእቅድ ስራው ስኬታማነት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑና እነዚህን አካላት በየግዜው ለማግኘትና ተሳትፎ አድርገው አስፈላጊውን ግብዓት ለማግኘት ሲባል ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስና ከዚያም በኃላ መረጃዎችን ለመለዋወጥና ለማጠናከርም የተመቻቸ ቦታ በማስፈለጉ የሆቴል አገልግሎት እንዲመቻች ተደርጓል፡፡

2.13.5. የኦዲተሩ አስተያየት፤

የውሎ አበል ክፍያ የሚፈጸመው ለሰራተኞች የምግብና መኝታ ወጪ እንዲሸፍን በመሆኑና የሰራተኞቹ ወጪ በሆቴል መስተንግዶ አገልግሎት የተሸፈነ በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ አግባብነት የለውም፡፡ በመሆኑም አላግባብ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.14. ሕጋዊ ባልሆነ የክፍያ ደረሰኝ (በተራ ፋክቱር) የተወራረደ የወጪ ሂሳብ፤

2.14.1. ግኝት፤

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 7 ለተገዛ እቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ማወራረጃ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ህጋዊና ኦርጂናል ደረሰኝ መሆን እንዳለበት ይገልፃል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በቀን 19/12/2012 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 194359 በለይቶ ማቆያ ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች የምግብ አገልግሎት ለሚውል የጤፍ ግዥ ለከፈለኝ የሺጥላ የእህል ንግድ ድርጅት ለተከፈለው ብር 215,000.00 ሕጋዊ የክፍያ ደረሰኝ መቅረብ ሲገባው በገቢዎች ሚኒስቴር እውቅና በሌለው ደረሰኝ (በተራ በፋክቱር) ሂሳቡ ተወራርዶ ተገኝቷል፡፡

2.14.2. ስጋት፤

ህጋዊ ባልሆነ ደረሰኝ ሂሳብ ማወራረድ የህግ ጥሰት በመሆኑ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ በተጨማሪም የአቅራቢዎች ገቢ እንዳይታወቅና የመንግስት ግብር በአግባቡ እንዳይከፈል መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

2.14.3. የማሻሻያ ሀሳብ፤

ክፍያዎች ሕጋዊ በሆኑ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች እንዲወራረዱ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

2.14.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ጊዜው የኮቪድ ወቅት በመሆኑና ዩኒቨርስቲው ከጅቡቲ ተመላሾችንና የአካባቢውን ማህበረሰብ በለይቶ ማቆያነት የሚያገለግለው ዩኒቨርስቲያችን ስለነበረና የምግብ አገልግሎት የሚያቀርበው ዩኒቨርስቲው በመሆኑ ድሬድዋ ላይ በዋጋ ማቅረቢያ ለመግዛት ህጋዊ ደረሰኝ ያላቸው በማጣታችን ወደ ተለያዩ የሃገሪቱ ክፍል

ባለሙያዎችን ልከን ባለመሳካቱ በለቀማ ግዥ አከናውነናል፡፡ ለወደፊቱ እርምት ወስደን የምናስተካክል መሆኑን እገልፃለን፡፡

3. **የተሰብሳቢ ሂሳብ፣**

3.1. **በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

3.1.1. **ግኝት፤**

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ "ለ" የስራ ማስኬጃ ቅድሚያ ክፍያ በ 7 ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበትና በንዑስ አንቀጽ "መ" ደግሞ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ መመሪያው ያመለክታል፡፡ በሰኔ 30/2013 የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት መሰረት በጊዜ ገደቡ መወራረድ ሲገባው ሳይወራረድ የቆየ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

- በሂሳብ መደብ 4201 (ልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያ) ብር 1,899,709.25 ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4211 (የግዢ ሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ) ብር 115,406.69 ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4251 (ለሥራ ተቋራጮች ቅድሚያ ክፍያ) ብር 25,617,693.79 ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4253 (ለአቅራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ) ብር 472,503.63 ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 28,105,313.36 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር** 9 ቀርቧል፡፡

3.1.2. ***ሥጋት፤***

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለው የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፤ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

3.1.3. የማሻሻያ ሀሳብ፤

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ፤ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ግን በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

- በ4201 ላይ የሚታየውን ሂሳብ ተከታትለን እንዲሰበሰብ የምናደርግ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- በ4211 ተመዝግቦ የሚታየው ሂሳብ ከግለሰቦቹ እንዲሰበሰብ በዩኒቨርሲቲያችን ህግ ክፍል አስፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ የተላለፈ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- በ4251 የሚታየው ለህንፃ ተቋራጮች የተከፈለ የቅድመ ክፍያ ሲሆን ተወራርዶ የሚያልቀው ፕሮጀክቶቹ ሲጠናቀቁ ስለሆነ በየጊዜው የፕሮጀክቶች አፈፃፀም መሰረት የሚቀነስ መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን፡፡
- በ4253 ላይ የሚታየው የቅድመ ክፍያ የዕቃ ከአቅራቢዎች ንብረቱ ገቢ እንደሆነ ተወራርዶ የሚጠናቀቅ መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

4. በጀት

4.1. የበጀት አጠቃቀም፤

4.1.1. ግኝት፤

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ለዩኒቨርሲቲው በበጀት ዓመቱ በየበጀት አርዕስቱ የተመደበው የተስተካከለ በጀት እና ስራ ላይ የዋለው በጀት ሲመዛዘን ከመደበኛ በጀት ብር 15,778,930.96 እና ከካፒታል በጀት ብር 221,507.50 በድምሩ ብር 16,000,438.46 ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት በጀት) ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 10** ቀርቧል፡፡

4.1.2. ሥጋት፤

የተፈቀደን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ አለማዋል በበጀት ዓመቱ በዕቅድ የተያዙ ስራዎች እንዳይከናወኑ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ በሌሎች መ/ቤቶች ሊሰራበት የሚችለውን በጀት በዩኒቨርሲቲው ስም ተይዞ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡

4.1.3. የማሻሻያ ሀሳብ፤

ዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስ አዋጅ መሰረት በስራ ላይ እንዲያውል እና ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ እንዳይሆን የተቋሙ ሥራ አመራር በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

4.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ምላሽ አልተሰጠም፡፡

5. ንብረት፤

5.1. የንብረት አያያዝና አመዘጋገብን በተመለከተ፤

5.1.1. ግኝት፤

የዩኒቨርሲቲው የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. **በቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤት (ዋናው ግቢ)፤**

- የቋሚ ዕቃ ንብረት ክፍል ሰራተኞች የራሳቸው ቢሮ የሌላቸውና በስቶር ውስጥ ስራቸውን የሚያከናውኑ መሆኑ፤
- አዲስ UPS ብዛት በቁጥር 70 ያለአገልግሎት ለረጅም ዓመት በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በ2011 ዓ.ም ገቢ የተደረጉ ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚውሉ አዲስ ዊልቼር ብዛት በቁጥር 5 ያለአገልግሎት በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በ2010 ዓ.ም ገቢ የሆኑ መቅረጫ በቁጥር 136፤ መቀስ በቁጥር 203፤ የወረቀት መብሻ በቁጥር 231፤ እስቴፕለር በቁጥር 67፤ እና የወረቀት መቁረጫ በቁጥር 10 ያለአገልግሎት በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- አዳዲስ ዕቃዎች እና የሚወገዱ ዕቃዎችና በአንድ ስቶር ተከማችተዉ የሚገኙ መሆናቸዉ፤

- ለቋሚ ዕቃዎች ቢንካርድ የተዘጋጀላቸው ቢሆንም በሚፈለገበዉ ቦታ ያልተቀመጠ መሆኑ እና አቀማመጡ ካይዘንን ያለተከተለ መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2. <u>**በአላቂ ዕቃዎች ግምጃ ቤት (ዋናው ግቢ)፤**</u>
   - የአላቂ ዕቃዎች ንብረት ክፍል ሰራተኞች የራሳቸው ቢሮ የሌላቸውና በስቶር ክፍል ውስጥ ስራቸውን የሚያከናውኑ መሆኑ፤
   - የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች፤ የደንብ ልብሶች እና የግንባታ እቃዎች በአላቂ ስቶር ተደባልቀው የተቀመጡ መሆኑ፤
   - በ2009 ዓ.ም ገቢ የሆኑ የውሃ ቧንቧ ዕቃዎች ዩኒየን ባለ 3 ኢንች ብዛት በቁጥር 130፤ ሪዲዩሰር ከ3 ወደ 1 ብዛት በቁጥር 290፤ ኢልቦው ብዛት በቁጥር 150 ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
   - በ2012 ዓ.ም ገቢ የተደረገ ኮላ ብዛት በቁጥር 680 ያለአገልግሎት በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
   - ለሻወር ቤት አገልፍግሎት የሚውሉ በርካታ ሽክላዎች ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
   - በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

3. <u>**በተመላሽ ዕቃዎች ግምጃ ቤት (ዋናው ግቢ)፤**</u>
   - አገልግሎት የማይሰጡ Pointer HP በቁጥር 36፤ Ponter Lexmark በቁጥር 9፤ Fax mashine በቁጥር 8፤ Printer በቁጥር 4፤ Desktop CRT/Moniter/ በቁጥር 66;LCD Moniter በቁጥር 50፤ Key bord በቁጥር 52፤ Prossesor በቁጥር 160፤ UPS በቁጥር 11፤ Lenovo laptop በቁጥር 10፤ Dell laptop በቁጥር 17 ፤Toshiba laptop በቁጥር 66፤ HP Laptop በቁጥር 78፤ LCD Projection Epson በቁጥር 4፤ LCD sony በቁጥር 20፤ Scaner በቁጥር 6፤ OK printer በቁጥር 55፤ Photo copy በቁጥር 17፤ የሻይ ማፍያ በቁጥር 7፤ ማከፋፈያ በቁጥር 350፤ ፍሪጅ በቁጥር 3፤ የስልክ ቀፎ በቁጥር 31፤ ቴሌቪዥን 43 ኢንች በቁጥር 5፤ ቴሌቭዥን 32 ኢንች በቁጥር 1፤ ሳምሰንግ የእጅ ስልክ በቁጥር 4፤

ዴል ታብሌት በቁጥር 50 ፍሬ ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜ በግምጃ ቤት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

5.1.2. ***ሥጋት፤***

የተጠቀሱት በንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የሚታዩ ግድፈቶች ለመንግስት ንብረት መጥፋትና መጉደል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

5.1.3. **የማሻሻያ ሀሳብ፤**

የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የታዩ የአሰራር ግድፈቶች እንዲስተካከሉ አፋጣኝ ተገቢ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

5.1.4. **የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

ቋሚ ንብረትን በተመለከተ፡-

- አዲስ UPS ብዛት በቁጥር 70 ያለአገልግት የተቀመጠ መሆናቸው የተገለጹ ቢሆንም በወቅቱ ተገዝቶ እንደመጣ ወጪ ያልተደረገ መሆኑ ቢገለፅም አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ ስለተረጋገጠ እንዲወገድ ከተያዙት ንብረቶች ጋር ተመዝግቦ ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርት የተደረገ ቢሆንም ኤሌክትሮኒክስን በኢኖቬሽን ሚንስተር በኩል እንዲወገድ በተደጋጋሚ በጹሁፍ የተጠየቁ ሲሆን አሁንም መፍትሄ ያልተገኘ መሆኑን እንገልፃለን፡፡ ይህ ይህ ጉዳይ ከአደገኛ ኬሚካል የሚያያዝ ስለሆነ እንደ ሀገር አቅጣጫ ተቀምጦ መፍትሄ ካልተፈለገለት በእኛ ደረጃ ሊወገድ እንደማይቻል ከዚህ በፊት የተፃፈልን ሰርኩርኩለር ደብዳቤ አያይዘን አቅርበናል፡፡
- በ2011 ዓ.ም ገቢ የተደረጉ ለአካል ጉዳተኞ አገልግሎት የሚውል አዲስ ዊልቸር በቁጥር 5 በግምጃ ቤት ውስጥ ተቀምጧል የተባለው ንብረቱን ያስገዛው ክፍል ወጪ አድርጎ ጥቅም ላይ እንዲያውል በሂደት ላይ ያለን መሆኑን እያሳወቅን በቅርብ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡
- በ2010 ዓ.ም ገቢ የሆኑ ንብረቶች እንደ መቅረጫ፤ መቀስ፣ የወረቀት መብሻ፣ እስቴፕለር፣ መቁረጫ በግምጃ ቤት የሚገኙ ንበረቶች ለተለያዩ ክፍል ሰራተኞች ወጪ በማድረግ ጥቅም ላይ እንዲውል እየተደረገ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

አላቂ እቃዎችን በተመለከተ፡-

- ተደበላልቆ ተቀምጧል የተባለው በስህተት ነው እንጂ ከእስቶክ ካርድ ጋራ ሲታይ በየራሱ ቦታ ላይ የተቀመጠ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

- የቢንቢ እቀዎችንና ተያያዥነት ያላቸውን እቃዎች ጥቅም ላይ ከሚውሉት ክፍል ጋር በመነጋገር ስራ ላይ እንዲውል እየተደረገ ይገኛል፡፡

6. **ልዩ ልዩ፤**

6.1. **በአስተዳደር ሥራ ላይ የተመደቡ መምህራንን በተመለከተ፤**

6.1.1. **ግኝት፤**

የፌዴራል የመንግስት የሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 በክፍል 3 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 3 ሰራተኞች መመደብ ያለባቸው የሥራ መደቡ የሚጠይቀውን ተፈላጊ ችሎታ የሚያሟሉና ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ጋር ተወዳድረው ብልጫ ያላቸው ሆነው ሲገኙ ብቻ መሆኑን ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- የአስተዳደር ዘርፍ የሥራ መደቦች በሙሉ የሥራ ጊዜ የሚከናወኑ ሥራዎች እንደመሆናቸው ተገቢውን የሰው ሀይል በቅጥር፤ በዕድገት ወይም በዝውውር መመደብ ሲገባ በዩኒቨርስቲው የአካዳሚክ አስተዳደር ጉዳዮች ተ/ኃላፊ እና የለውጥና መልካም አስተዳደር ተ/ዳይሬክተር የአካዳሚክ ባለሙያዎች (መምህራን) ሆነው በተጠቀሱት የሥራ መደቦች ላይ በተደራቢነት በኃላፊነት እያገለገሉ የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

6.1.2. **ስጋት፤**

ቋሚ የአስተዳደር የስራ መደቦች በአካዳሚክ ባለሙያ (በመምህራን) በተደራቢነት እንዲያዙ ማድረግ የየክፍሎቹ ሥራዎች በወቅቱና በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዳይከናወኑ ያደርጋል፡፡

6.1.3. **የማሻሻያ ሃሳብ፤**

በቋሚ የአስተዳደር የስራ መደቦች ላይ በተደራቢነት ተመድበው የሚሰሩ የአካዳሚክ (መምህራን) ምደባ መመሪያውን ያልተከተለ በመሆኑ የሰራተኞች ምደባ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

6.1.4. **የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

በዩኒቨርስቲው ውስጥ በአካዳሚክ እንዲሸፈኑ የተደረጉ መደቦች በተደጋጋሚ የውጭና የውስጥ የቅጥር ማስታወቂያዎች ቢወጡም መደቡ የሚጠይቀው መስፈርት ሟሟላት ባለመቻለቸው ቅጥር መፈፀም ሳይቻል በመቅረቱ ስራ እንዳይስተጓጎል በማሰብ መደቦቹ በአካዳሚክ አስታፍ እንዲሸፈኑ ተደርጓል፡፡

7. የክትትል ኦዲት (Follw-up Audit)፤

7.1. እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ግኝቶች፤

7.1.1. ግኝት፤

ባለፉት በጀት ዓመታት የኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

እርምጃ ሊወሰድበት የሚገባ			እርምጃ የተወሰደበት			እርምጃ ያልተወሰደበት		
በገንዘብ መጠን	በቁጥር	በፐርሰንት (በ%)	በገንዘብ መጠን	በቁጥር	በፐርሰንት (በ%)	በገንዘብ መጠን	በቁጥር	በፐርሰንት (በ%)
5,143,601.14		100%	--		--	5,143,601.14		100%
	14	100%		--	--		14	100%

በኦዲት አስተያየቱ መሰረት በቁጥር ደረጃ ከተገለጹት የአሰራር ክፍተቶች ውስጥ 100% ላይ የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በገንዘብ ደረጃም እርምጃ ሊወሰድበት ከሚገባው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ውስጥ 100% ላይ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

የ2012 በጀት ዓመት ግኝቶች፤

- የአስተዳደር ሰራተኞች ከመደበኛ ስራቸው ውጭ በተማሪዎች ምረቃ ዝግጅት ስለተሳተፉ በሚል ሰራተኞቹ ለስራ ጉዳይ ከሚሰሩበት ቦታ ወደ ሌላ ባልሄዱበት ሁኔታ ብር 159,000.00 አላግባብ የውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሳይፈቅድ ለአስተዳደር ሰራተኞች በድምሩ ብር 1,035,023.40 የትርፍ ሰአት ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤
- ለትምህርት ውጭ ሃገር ለተላኩ መምህራን በየወሩ ግማሽ ደመወዝ መከፈል ሲገባዉ አላግባብ ብር 135,698.15 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
- አገር ውስጥ ለሚማሩ መምህራን ድጋፍ ክፍያ መከፈል ከሚገባው በላይ ብር 8,400.00 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
- ለመምህራን በመመሪያው መሰረት ክፍያ መፈጸም ሲገባ ከተመን በላይ ጭማሪ በማድረግ በድምሩ ብር 139,440.00 አላግባብ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
- በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤

የ2011 በጀት ዓመት ግኝቶች፤

- የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዝዳንትና ም/ፕሬዝዳንቶችን በማስመረጥ ሂደት ውስጥ ለተሳተፉ ኮሚቴ አባላት ብር 91,800.00 እና ለ5 የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ብር 71,680.00 በድምሩ ብር 163,480.00 ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲውን ለለቀቁ ሰራተኛ (ወ/ሮ አፍሪካ ደጀኔ) ከመስከረም እስከ ሚያዚያ በድምሩ ብር 30,115.20 የደመወዝ ክፍያ አላግባብ የተከፈላቸው መሆኑ፤
- በዋና ግቢ ለተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ለተለያዩ አቅራቢዎች (ድርጅቶች) ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበው ብር 4,041,343.14 የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ፣

የ2010 በጀት ዓመት ግኝቶች፤

- ከእንግዳ መምህራን ክፍያ 30% (ሰላሣ በመቶ) የገቢ ግብር መቀነስ ሲገባው 2% (ሁለት በመቶ) ብቻ በመቀነሱ በዋናው ግቢ ብር 197,407.64 እና በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ብር 109,217.00 በድምሩ ብር 306,624.64 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
- በሲኢቢ (CEB) ቤተ መፅሃፍት 5 የኮምፒዩተር RAM መጥፋታቸው ከክፍሉ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣
- ከተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር ለአስተዳደርና ልማት ም/ፕሬዚዳንት እና ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በተፃፈ ደብዳቤ በተማሪዎች መኝታ ቤት በነሐሴ 2009 ዓ.ም እና በመስከረም 2010 ዓ.ም ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ዕረፍት መሄዳቸውን እና የክረምት ተማሪዎች ትምህረት መጨረሳቸውን ተከትሎ 225 ፍራሾች እና ሁለት 32 ኢንች ቴሌቪዥኖች መጥፋታቸው የተገለጸ መሆኑ፣
- ከቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ እና ባለሙያዎች ጋር በጋራ የኦዲት ቡድኑ በንብረት አካላዊ እይታ ወቅት በብሎክ ቁጥር 22 ባለ ሦስት ፌዝ ከ200 ሜትር በላይ የሚረዝም ኬብል ተቆርጦ መጥፋቱ የተገለጸ መሆኑ፤
- ከምህንድስና ክፍል በቁጥር ድ/ዳ/ዩ/ምቡ/01013/2010 በቀን 26/2010 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ ማከሚያ ማዕከል ትልቅ SDB የብረት በሮች በቁጥር 45 እና የዊንግ ዶርሚተሪ 2 ህንጻ እድሳት ላይ እያሉ የተለያዩ የኤሌትሪክ ፊክስቸሮች (Breakers) መጥፋታቸው የተገለጸ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

ከላይ የተዘረዘሩት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያሳሰብን ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም። **ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 11 ቀርቧል።**

7.1.2. ሥጋት፤

በተሰጠ የኦዲት አስተያየት መሠረት የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ በኦዲት ወቅት የታዩ የአሰራር ግድፈቶች እንዳይታረሙ ከማድረጉም ባሻገር ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

7.1.3. የማሻሻያ ሀሳብ፤

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

7.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የዩኒቨርሲቲያችን አመራሮች በቅርቡ በአዲስ መልኩ የተዋቀሩ ሲሆን አመራሩም ዩኒቨርሲቲው ያለውን ክፍተት እየለዩ ተገቢውን የማስተካከያ እርምት እርምጃ እየወሰደ ሲሆን በኦዲት የተነሱትንም ግኝቶች አዲሱ አመራር በተገቢው መንገድ ማጣራት እያደረገ ሲሆን የተቀመጡትንም የመፍትሄ ሀሳቦች በተገቢው መንገድ አጣርቶ ወደፊት የወሰደውን እርምጃና የመፍትሄ አቅጣጫ በደብዳቤ የምናሳውቅ መሆኑን እየገለፅን በዩኒቨርሲቲያችን አመራሮች በአጭር ጊዜ በመቀያየራቸው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን እንድትገነዘቡልን እንጠይቃለን፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን!

አባሪ 1፡ ከግዢ ክፍያ ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ (ያልተሰበሰበ) የቅድሚያ ግብር፤

ተ.ቁ	ቀን	የባ/ወ/ማ/ቁ	አገልግሎት የሰጠው ድርጅት	የቀረበው አገልግሎት	የተከፈለው ገንዘብ መጠን	ያልተቀነሰ ዊዝሆልዲንግ
1	19/04/13	196518	ፍሪ ዱቄት ፋብሪካ	የዳቦ ዱቄት	194,400.00	3,888.00
2	07/04/13	196477	››	››	190,800.00	3,816.00
					ድምር	7,704.00

አባሪ 2፡ ያልተሰበሰበ (ተቀናሽ) ያልተደረገ የገቢ ግብር

ተ.ቁ	ቀን	የባ/ወ/ማ/ቁ	የወጪው ምክንያት	የተከፈለ የገንዘብ መጠን	2% የተቀነሰ	መቀነስ የነበረበት (30)%	ልዩነት
1	03/06/13	196879	ለአዲስ አበባ ጉዳይ ማስፈፀሚያ የቢሮና የእንግዳ ማረፊያ ያለው ከወ/ሮ ሙሉ ለገሰ ለአንድ አመት	480,000.00	9,600.00	144,000.00	134,400.00
2	29/10/13	193388	ለጤና ሳይንስ ተማሪዎች አገልግሎት የሚውል የቤት ኪራይ ከወ/ሮ ፎዚያ አዱስ 01/11/12 እስከ 30/10/13	642,000.00	12,840.0	192,600.00	179,760.00
3	16/7/13	197420	ዩንቨርስቲው ለእንግዳ ማረፍያ አገልግሎት የሚውል ቤት ከወ/ሮ ዮዲት ማሞ 1/6/13 30/5/14	168,000.00	3,360.00	50,400.00	47,360.00
						ድምር	361,520.00

አባሪ 3፡ ለጊዚያዊ ሰራተኞች የተፈጸመ ክፍያ፤

ተ.ቁ	ቀን	የባ/ወ/ማ/ቁጥር	የስራው አይነት	የሰራተኞች ብዛት	የገንዘብ መጠን
1.	27/02/13	675592	የተማሪዎች ምግብ ቤት ሰ/ክፍያ	30	54,480.00
2.	27/02/13	675593	›› ››	30	53,940.00
3.	27/01/13	675573	›› ››	61	111,000.00
4.	12/01/13	675570	›› ››	64	19,380.00
5.	28/12/12	675565	›› ››	61	109,320.00
6.	26/05/13	582929	›› ››	29	50,220.00
7.	30/04/13	582919	›› ››	28	51,180.00
8.	30/03/13	582908	›› ››	30	55,080.00
9.	05/12/12	675560	ጠቅላላ አገልግሎት	51	71,490.00
10.	29/11/12	675557	የተማሪዎች ምግብ ቤት ሰ/ክፍያ	61	110,340.00
11.	07/03/13	194933	የጠቅላላ አገልግሎት ሰ/ክፍያ	42	59,910.00
12.	06/04/13	582912	›› ››	32	54,210.00
13.	06/04/13	196470	›› ››	33	51,780.00
14.	06/05/13	5829/22	›› ››	36	57,060.00
15.	05/06/13	582939	›› ››	45	75,420.00
16.	04/07/13	582950	ቤተ መጽሃፍት ሰ/ክፍያ	43	74,070.00
17.	05/08/13	583563	ጠቅላላ አገልግሎት ሰ/ክፍያ	36	63,780.00
18.	01/07/13	582949	የተማሪዎች ምግብ ቤት ሰ/ክፍያ	29	51,900.00
19.	02/09/13	583575	ጠቅላላ አገልግሎት ሰ/ክፍያ	31	55,440.00
20.	05/10/13	583593	ጠቅላላ አገልግሎት ሰ/ክፍያ	42	75,000.00
21.	03/10/13	583589	የተማሪዎች ምግብ ቤት ሰ/ክፍያ	31	54,157.00
22	04/07/13	583551	ጠቅላላ አገልግሎት ሰ/ክፍያ	43	75,180.00
				ድምር	**1,439,337.00**

አባሪ 4፡ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሳይፈቅድ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፤

1. በዋናው ግቢ፤

ተ.ቁ	ቀን	የቫውቸር አይነት	የቫውቸር ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የክፍያው ምክንያት	የገንዘብ መጠን
1	09/09/13	JV	583580	6116	በዩንቨርስቲው የግቢ ፀጥታ ደህንነት ክፍል ሰራተኞች የጥርና የካቲት ወር 2013 ዓ.ም በማኔጅመት ውሳኔ መሰረት ትርፍ ሰዓት ክፍያ	73,084.03
2	16/09/13	JV	197797	6116	በዩንቨርስቲው የግቢ ፀጥታ ደህንነት ክፍል ሰራተኞች የጥር ወር 2013 ዓ.ም በማኔጅመት ውሳኔ መሰረት ትርፍ ሰዓት ክፍያ	66,816.06
3	26/04/13	JV	196537	6116	በዩንቨርስቲው የግቢ ፀጥታ ደህንነት ክፍል ሰራተኞች የመስከረም ወር 2013 ዓ.ም ትርፍ ሰዓት ክፍያ	78,533.23
4	14/03/13	JV	675125	6116	በዩንቨርስቲው የግቢ ፀጥታ አገልግሎት በተዓፊ ደብዳቤ የጥበቃ ሰራተኞች የጥቅምት ወር 2013 ትርፍ ሰዓት ክፍያ	82,898.55
5	12/04/13	JV	196493	6116	በዩንቨርስቲው የግቢ ፀጥታ አገልግሎት በተዓፊ ደብዳቤ የጥበቃ ሰራተኞች የህዳር ወር 2013 ዓ.ም ትርፍ ሰዓት ክፍያ	58,664.2
6	04/01/13	JV	194113	6116	በዩ የጥበቃ ሰራተኞች የህዳር ወር 2013 ዓ.ም ትርፍ ሰዓት ክፍያ	58,291.09
					ድምር	**418,287.16**

2. በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፤

ተ.ቁ	ቀን	ሂ.መ	ደረሰኝ ቁጥር	የወጪ ምክንያት	የገንዘብ መጠን
1.	30/08/13	6116	207223	Self level evaluation of Industrial Engineering program	106,999.92
2.	30/06/13	6116	207224	Self level evaluation of construction Technology and management program	106,699.92
3	28/04/13	6116	208586	Self level evaluation of Textile Engineering program	105,899.63
2.	26/04/13	6116	208572	Self level evaluation of Architecture Program	99,999.90
3.	26/04/13	6116	208571	Self level evaluation of chemical Engineering	108,499.68
4.	26/04/13	6116	208574	Self level evaluation of process Engineering	109,499.97
5.	30/05/13	6116	207336	Self level evaluation of mechanical Engineering	121,499.88
6.	30/05/13	6116	207337	Self level evaluation of computer science program	109,499.88
7.	29/07/13	6116	207421	Self level evaluation of school of civil Engineering and Architecture/CoTM/	103,999.92
8.	30/06/13	6116	207222	Self evaluation of school of Electrical and Computer Engineering	108,199.88
				ድምር	**1,080,798.58**

አባሪ 5፡ ለማስተባበር ሥራ፤ በኮሚቴ ለተሳተፉ እና የተማሪዎች መረጃ ለመዘገቡ የተፈጸመ ክፍያ፤

ተ.ቁ	ቀን	የባ/ወ/ ማ/ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የክፍያው ምክንያት	የገንዘብ መጠን
1	22/10/13	198295	6251	በአዲስ መልክ የተዘጋጁ የጨረታ ሰነዶችን በተለያየ ሂደት ሲገመግም እና ሲያፀድቅ በቆየበት ግዜ በትጋትና በቅን ልቦና ለሰሩ የኮሚቴ አባላት በሚል ከ84.-108 ሰዓት በሰዓት ከብር 100-120.00 በማሰብ በድምር ብር 55,920.00	55,920.00
2	26/01/13	194813	6251	ለተማሪዎችና ሰራተኞች የዲሲፕሊን ኮሚቴ አባላት በሚል ለ3 ኮሚቴዎች በሰዓት ብር 100.00 በማሰብ ለ355 ሰዓት በድምር ብር 35,500.00 የተከፈላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡	35,500.00
3	26/01/13	0963538	6271	የፋይናንስ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት የውስጥ መመርያ ላዘጋጁ 9 ኮሚቴዎች ለያንዳንዳቸው ከብር 2,000.00 እስከ 5,000.00 በድምር 27,000.00 ብር የተከፈለ ሲሆን ክፍያው የክፍያ ተመን ያልወጣለት በመሆኑ አግባብነት የለውም፡፡	27,000.00
4	25/12/12	194430	6251	ነሀሴ 16/2012 ዓ.ም በተማሪዎች ምረቃ ላይ ላስተባበሩ 5 ሰራተኞች በሚል ለያንዳንዳቸው 2,000.00 ለ5 ሰራተኞች በድምር ብር 10,000.00 የተከፈለ፤	10,000.00
5	15/12/12	194240	6251	የሲምስ/SIMS/ ስራ በመደኛ ሥራ የሚከናወን ሆኖ ሳለ የተፈጸመ ክፍያ፡- • ለ30 የባዮግራፊ እና ግሬድ ኢንኮድ ላደረጉ ሰራተኞች በድምር ብር 313,636.00 የተከፈለ፤ • ለ12 ኃላፊዎች የገባውን መረጃ ትክክለኛነት በማረጋገጥ ያፀደቁ የኮሌጅ ሬጅስትራር ኃላፊዎች በድምር ብር 67,819.00 የተከፈለ፤ • ለ22 የመረጃ አቅራቢ የሬጅስትራር ሪከርድ ክፍል ሰራተኞች የተከፈለ በተማሪ 3.00 ብር በድምር ብር 37,965.00 የተከፈለ፤ • ለ35 ካሪኩለም ወደ ሲስተም አስገብቶ ያፀደቁ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ለያንዳንዳቸው 20 ሰዓት በብር 180.00 በድምር ብር 126,000.00 የተከፈለ፤ • ለ22 ኃላፊዎች ካሪኩለሞችን በማፅደቅ /SIMS/ ስራዎችን ክትትል እና ድጋፍ ያደረጉ አካላት ክፍያ ለያንዳንዳቸው 20 ሰዓት በብር 180.00 በድምር ብር 79,200.00 የተከፈለ፤ • ለ4 የቴክነክ ኮሚቴ አባላት የገባውን የተመረቁ ተማሪዎች መረጃ ትክክለኛነት በማረጋገጥ ያፀደቁ ለያንዳንዳቸው 1,000.00 ብር በድምር ብር 4,000.00 የተከፈለ፤ • ለ4 የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ለያንዳንዳቸው 60 ሰዓት በብር 180.00 ብር በማሰብ ድምር ብር 43,200.00 የተከፈለ ሲሆን በአጠቃላይ በድምር ብር 671,820.00 በማኔጅመት ውሳኔ መሰረት የተከፈለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡	671,820.00
				ድምር	**800,240.00**

አባሪ 6፡ ከመመሪያ ውጭ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ፤

ተ.ቁ	ቀን	የሂሳብ መደብ	የባ/ወ/ማ/ ቁጥር	የክፍያው ምክንያት	የተከፈለው ግለሰብ	የገንዘብ መጠን
1	09/06/13	6231	196904	የጥር ወር እሁድና ቅዳሜ ለሰሩት	ለፋይናንስ ክፍል ሠራተኞች	59,901.80
2	10/06/13	6231	196892	የጥር ወር እሁድና ቅዳሜ ለሰሩት	ለግዢ ክፍል ሰራተኞች	55,068.00
3	26/05/13	6231	196816	የታህሳስ ወር እሁድና ቅዳሜ ለሰሩበት	የሰው ሃብት ስራ አመራር ክፍል	13,557.60
4	18/01/13	6231	194639	የነሐሴ 2012 እሁድና ቅዳሜ ለሰሩበት	ለግዢ /ን/ አስተዳደር ክፍል ሰራተኞች	22,436.80
5	06/0413	6231	196367	ከመስከረም እስካ ህዳር እሁድና ቅዳሜ ለሰሩበተ	የጠቅላላ አገልግሎት ክፍል ሠራተኞች	173,861.40
6	14/05/13	6231	196595	የታህሳስ ወር እሁድና ቅዳሜ ለሰሩበት	በአስ/ተማ/አገ/ም/ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ስር ሰራተኞች	45,824.40
7	12/12/12	6231	194233	የሃምሌ ወር ቅዳሜና እሁድ ለሰሩበት	ኦዲት እና ኢንስፔክሽን ሰራተኞች	52,513.20
8	05/13/12	6231	0963616	የነሐሴ ወርቅዳሜና እሁድ	የአስተዳደር ሰራተኞች	12,555.00
9	23/09/13	6231	198003	ሚያዝያ ወርቅዳሜና እሁድ	የአስተዳደር ሰራተኞች	115959.00
10	14/08/13	6231	197656	የመጋቢት ወርቅዳሜና እሁድ	አስተዳደር ሰራተኞች	70,251.60
11	10/07/13	6231	197406	የካቲት ወር ቅዳሜና እሁድ	አስተዳደር ሰራተኞች	80541.60
12	08/07/13	6231	197401	የካቲት ወር ቅዳሜና እሁድ	ፋይናንስ ሰራተኞች	52,164.00
13	21/10/13	6231	198222	የግንቦት ወር ቅዳሜና እሁድ	ለአስተዳደር ሰራተኛች	62,610.00
					ድምር	**817,244.40**

አባሪ ቁጥር 7፡ ከዕቃ አቅራቢዎች ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ፤

ተ.ቁ	ቀን	የባ/ወ/ማ/ቁ	ሂሳብ መደብ	የእቃው አይነት	የአቅራቢው ሙሉ ስም	የውሉ ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ተ.እ.ታክስ ጨምር/1/	ውል የተገባበት ቀን	ውሉ የሚያበቃበት ቀን	ንብረቱ ገቢ የተደረገበት ቀን	የዘገየበት ቀን ብዛት/2/	የጉዳት ካሳ (1*2*0.001)
1	23/10/13	198244	6211	ሴፍት ጫማ፣ አጭር ቡትስ ቆዳ፣ የሴት ጫማ	ገ/መስቀል አበራ የግንድላ የጣውላ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ችርቻሮ ንግድ	119,370.00	19/8/13	19/9/13	11/10/13	22	2,626.14
2	21/10/13	193358	6211	ጃኬት፣ ቀበቶ	ብሩክ ሙሉጌታ ወ/አማኤል የጫማ እና የቆዳ ውጤቶች ጅምላ ንግድ	930,988.71	19/8/13	19/9/13	8/10/13	19	17,688.78
3	18/10/13	193353	6211	ፍራሽ	ዘሀራ ሰይድ ጅምላ ንግድ	5,929,399.93	13/8/13	13/9/13	7/10/13	24	142,305.59
4	28/10/13	193385	6211	ለሰራተኞች ደንብ ልብስ	ቢቲ ትሬዲንግ ሀ/የተ/የግ/ማህበር	1,324,291.77	21/8/13	21/9/13	24/10/13	33	43,701.62
5	29/10/13	193389	6211	ለሰራተኞች ደንብ ልብስ	ፍሉድ ትሬዲንግ ሀ/የተ/የግ/ማህበር	1,836,349,.09	15/8/13	15/9/13	24/10/13	39	71,617.61
6	24/10/13	193376	6211	ካፖርት ፣ዝናብ ልብስ	ፋህሚ መሀመድ ጨርቃ ጨርቅና ስፌት	451,783.60	21/8/13	21/9/13	17/10/13	26	11,746.37
7	21/7/13	197275	6215	ቶርሽን ጫማ	ኤ.አር.ቲ ትሬዲንግ ሀ/የተ/የግ/ማህበር	139,200.00	26/4/13	26/5/13	16/6/13	20	2,784.00
8	29/7/13	197559	6244	ሎከር	ማህበረ ትጉሃን የእንጨት ብረታ ብረት ኮንስትራክሽን ስራ	1,694,801.00	15/4/13	14/5/13	17/7/13	17	28,811.61
9	30/8/13	197770	6241	የመኪና ዕቃ መለዋወጫ	ኤርሚያስ ገረመው የመኪና ዕቃ መለዋወጫ	2,622,449.00	20/4/13	20/5/13	01/8/13	100	262,244.90
										ድምር	**583,526.62**

አባሪ 8፡ በዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) ተከፋፍሎ የተፈጸመ ግዢ፤

1. በዋናው ግቢ፤

ተ.ቁ	ቀን	የሳብ መደብ	የቫውቸር ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የተገዛበት ድርጅት ስም	የገንዘብ መጠን
1	09/04/13	6244	196490	ቁልፍ ለተማሪዎች መኖሪያ የሚውል	መሀመድ ኡመር አቡባከር የህንጻ መሳሪያ	161,920.00
2	09/06/13	6244	196891	ሲሊንደር ቁልፍ ከነካሴቱ	መሀመድ ኡመር አቡባከር የህንጻ መሳሪያ	157,492.50
3	18/02/13	6244	675605 /JV/	ለተማሪዎች ዝግጅት ምዕራፍ አገልግሎት የሚውል ሙሉ ሴት ቁልፍ	አብዱረህማን አህመድ የህንጻ መሣሪያዎች መሸጫ	146,912.50
4	17/02/13	6244	675604 /JV/	ለተማሪዎች ዝግጅት ምዕራፍ አገልግሎት የሚውል ቁልፍ ከነካሴቱ	አብዱረህማን አህመድ የህንጻ መሣሪያዎች መሸጫ	126,224.00
5	27/01/13	6214	194542	ለጥገና ስራ የሚዉል ክሮን ጌት ቫልቭ	መሀመድ ኡመር አቡባከር የህንጻ መሳሪያ መሸጫ	122,360.00
6	25/03/13	6244	196362	ዶርሚተሪ ሽንት ቤት ጥገና አገልግሎት የሚውል ማጠፊያ(ቶርኖ)፤ኤሌክትሮድእና Girinding	አብዱረህማን አህመድ የህንጻ መሣሪያዎች መሸጫ	107,766.00
7	17/05/13	6244	196687	ውሃ ጉድጓድ የሚውል ጋልቫናይዝድ የውሃ ፓይፕ	አህመድ አብዱረህማን ጃሚ ጄኔራል ትሬዲንግ	96,600.00
8	21/04/13	6218	196384	የሽንት ቤት ማፅጃ ሀይድሮክሎሪክ አሲድ	ከራንኬም ኢንዱስትሪ ኤንድ ትሬዲንግ	58,499.35
9	22/04/13	6218	196530	ኦሞ/የዱቄት ሳሙና/	ወሂብ ኡመር ኡስማኤል ሸቀጣቀጥ መደብር	67,562.50
10	30/04/13	6218	196396	ፕላስቲክ ጎንት እና ዘንባባ መጥረጊያ	አብዱሰመድ አብዱራህማን አንሳር	170,039.00
11	09/02/13	6212	194904	ደብተርና እስክርቢቶ	ኦሪዮን የጽህፈት መሳሪያመደብር	136,620.00
12	28/05/13	6215	196875	ደብተርና እስክርቢቶ	ኦሪዮን የጽህፈት መሳሪያመደብር	64,400.00
13	16/04/13	6212	196379	A4ወረቀት ግዥ	ኦሪዮን የጽህፈት መሳሪያ መደብር	163,875.00
14	17/05/13	6212	196709	A4ወረቀት ግዥ	ዳዊት ግርማ የፅህፈት መሳርያ	181,125.00
15	09/02/13	6314	194903	የኤሌክትሪክ እቃዎች	ፈረድ መሀመድ የኤሌክትሪክ እቃዎች መሸጫ	165,887.50
					ፈረድ መሀመድ	

16	12/02/13	6314	194910	የኤሌክትሪክ እቃዎች	የኤሌክትሪክ እቃዎች መሸጫ	82,340.00
17	16/04/13	6313	196509	ፋይበር ግላስ ሮቶ	አብዱረህማን አህመድ የህንፃ መሳርያ	144,900.00
18	18/03/13	6313	196352	የኤሌክትሪክ እቃዎች	በድሶሪ በክሪ ኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ መደብር	153,410.00
19	29/06/13	6314	197070	የመሬት ምንጣፍ	ኤልሳቤት ሰለሞን የቤትና የቢሮ ማስዋብያ	89,125.00
20	01/05/13	6314	196581	የመሬት ምንጣፍ	ፍቅር አወላቸዉ	25,875.00
21	28/09/13	6215	198016	የእስፖርት እቃዎች	ጎ ቴዲ እስፖርት	197,799.98
22	08/07/13	6213	197402	የተመራቂ ተማሪዎች ባይንደር	ሀ ግዕዝ ህትመትና ማስታወቂያ	197,136.00
23	26/08/13	6213	197768	ማስታወሻ ደብተር የዩኒቨርሲቲ ሎግ የታተመበት	ሀ ግዕዝ ህትመትና ማስታወቂያ	54,809.00
24	1/08/13	6218	197294	የእቃ ማጠቢያ ፈሳሽ ሳሙና	እንቻለው ተስፋዬ የፅዳታ እቃዎች መሸጫ	198,720.00
25	02/07/13	6212	197076	ለፎቶ ኮፒ ና ለህትመት አገልግሎት የሚውል ቀለም	ኦሜዳድ ሀ/የተ/የግል/ማህበር	199,082.25
26	27/07/13	6213	197286	ብራንድ ጋይድ ላይን	አአደ ቬንቸር ህትመትና ማስታወቂያ ስራ ሀ/የተ/የግል/ማህበር	200,000.00
27	26/10/13	6314	193515	አረብያን መጆሊስ ገስት ሀዉስ	አብዱልሃፊዝ ሙርሲል	97585.71
28	19/19/13	6314	197951	የመሬት ምንጣፍ	ኤልሳቤት ሰለሞን አበበ የቤትና ቢሮ ማስዋብያ ድርጅት	93,437.50
					ድምር	**3,661,503.79**

አባሪ 9፡ በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

ተ.ቁ	የሂሳብ መደብ	የቆይታው ጊዜ			ድምር
		ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት የቆየ	ከ5 ዓመት በላይ እስከ 10 ዓመት የቆየ	ከ10 ዓመት በላይ የቆየ	
1	4201	1,899,709.25			1,899,709.25
2	4211	115,406.69			115,406.69
3	4251	25,617,693.79			25,617,693.79
4	4253	472,503.63			472,503.63
	ድምር	**28,105,313.36**			**28,105,313.36**

አባሪ ቁጥር 10፡ የ2013 በጀት ዓመት በጀት ማመዛዘኛ፤

1. ከመደበኛ በጀት ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት) በጀት፤

የሂሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ ወጪ	ልዩነት	
			ያልተሰራበት በጀት	መቶኛ (%)
6113	690,400.00	486,706.96	203,693.04	30%
6123	114,400.00	84,297.98	30,102.02	26%
6133	80,000.00	44,280.33	35,719.67	45%
6213	2,425,500.00	1,848,889.55	576,610.45	24%
6214	1,291,658.00	834,312.37	457,345.63	35%
6215	14,091,408.00	12,361,604.98	1,729,803.02	12%
6218	3,123,300.00	1,245,848.95	1,877,451.05	60%
6219	3,056,200.00	1,964,487.67	1,091,712.33	36%
6223	4,532,700.00	937,783.65	3,594,916.35	79%
6232	7,388,700.00	6,615,324.90	773,375.10	10%
6254	1,117,200.00	838,398.71	278,801.29	25%
6255	139,200.00	30,390.25	108,809.75	78%
6256	600,000.00	484,697.65	115,302.35	19%
6258	4,226,500.00	3,581,788.09	644,711.91	15%
6259	3,765,400.00	2,508,114.17	1,257,285.83	33%
6271	8,310,900.00	7,322,511.90	988,388.10	12%
6272	250,000.00	0.00	250,000.00	100%
6314	6,379,390.00	5,243,986.93	1,135,403.07	18%
6412	2,149,500.00	1,520,000.00	629,500.00	29%
ድምር	**63,732,356.00**	**47,953,425.04**	**15,778,930.96**	

2. ከካፒታል በጀት ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት) በጀት፤

ሂሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ ወጪ	ልዩነት	
			ያልተሰራበት በጀት	መቶኛ (%)
6231	150,000.00	11,422.50	138,577.50	92%
6232	150,000.00	67,070.00	82,930.00	55%
ድምር	**300,000.00**	**78,492.50**	**221,507.50**	

አባሪ ቁጥር 11፡ በ2012/2011/2010 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች፤

ተ.ቁ	የ2012 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች	እርምጃ		የተወሰደው እርምጃ	የኦዲተር አስተያየት
		ከተወሰደ	ካልተወሰደ		
		✓	X		
1	የአስተዳደር ሰራተኞች ከመደበኛ ስራቸው ውጪ ለተማሪዎች ምረቃ ዝግጅት ላደረጉ በሚል ለ96 ሰራተኞች መንግስት በፈቀደው የውሎ አበል ተመን ብር 171፤218 እና 214 የቁርስ፣ ምሳ እና እራት ለእያንዳንዳቸዉ ለ20 ቀን በማድረግ ብር 159,000.00 ሰራተኞቹ ለስራ ጉዳይ ከሚሰሩበት ቦታ ወደ ሌላ ባልሄዱበት ሁኔታ አለአግባብ በውሎ አበል ተመን መሰረት ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡		X	ተመላሽ ለመሆኑ ማስረጃ አልቀረበም፡፡	በሪፖርት ይገልጽ፡፡
2.	ዩኒቨርሲቲዉ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ሳያስፈቅድ በማናጅመንት ዉሳኔ ብቻ ለአስተዳደር ሰራተኞች በድምሩ ብር **1,035,023.40** የትርፍ ሰአት ክፍያ የፈፀመ መሆኑ፤		X	በ2013 በጀትም ተመሳሳይ ግኝት ተገኝቷል፡፡	በሪፖርት ይገልጽ፡፡
3.	ለትምህርት በመንግሥት ወደ ውጭ ሃገር ተልከው ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሠራተኞች ደመወዝ አከፋፈልን በተመለከተ፣ ከአንድ ወር በላይ ለሆነ ጊዜ የሚሄዱት ከተፈላጊ መረጃዎች ጋር ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ሲፈቀድ በየወሩ ግማሽ ደመወዛቸው እንደሚከፈላቸው መመርያው በየወሩ ግማሽ ደመወዝ ቢያዝም መከፈል ሲገባዉ አላግባብ **በጠቅላላው ድምር ብር** 135,698.15 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤		X	መመለሱን የሚገልጽ ማስረጃ አልቀረበም፡፡	በሪፖርት ይገልጽ፡፡
4	አገር ውስጥ ለሚማሩ መምህራን የድጋፍ ክፍያን በተመለከተ፡-ከሰው ሀብት የሥራ ሂደት በተሰጠን መግለጫ መሰረት ሄኖክ መላኩ ደምሴ ድሬዳዋ እየተማሩ አዲስ አበባ ሲማሩ የሚከፈለውን ክፍያ በመክፍል ከሀምሌ 2011 እስከ ሰኔ 2012 ዓ.ም የአስራ ሁለት ወር በተመደበላቸዉ የድጋፍ ተመን መሰረት ብር 7,800.00 መከፈል ሲገባዉ አላግባብ ብር 16,200.00 በመከፈሉ በብልጫ ብር 8,400.00 የተከፈለ መሆኑ፤		X	ተመላሽ ለመሆኑ ማስረጃው አልቀረበም፡፡	በሪፖርት ይገልጽ፡፡

5	ለመምህራን ከተመን በላይ የተከፈላቸዉ ክፍያን በተመለከተ በመመርያው መሰረት ክፍያ መፈጸም ሲገባ ከተመን በላይ በልዩነት ጭማሪ በማድረግ በድምሩ ብር 139,440.00 አላግባብ ከመመሪያ ውጪ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤		X	ገንዘቡ ተመላሽ ለመደረጉ ማስረጃ አልቀረበም፡፡	በሪፖርት ይገልጽ፡፡
6	በመመሪያው መሠረት በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤		X	በ2013 በጀት ዓመትም ተመሳሳይ ግኝት ተገኝቷል፡፡	በሪፖርት ይገልጽ፡፡
	የ2011 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች				
7	የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዝዳንትና ም/ፕሬዝዳንቶችን በማስመረጥ ሂደት ውስጥ ለተሳተፉ ኮሚቴ አባላት ብር 91,800.00 ለ5 የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ በድምሩ ብር 71,680.00 በአጠቃላይ ድምር ብር 163,480.00 ከደንብና መመሪያ ውጭ መከፈሉ፣		X	ገንዘቡ ተመላሽ ለመደረጉ ማስረጃ አልቀረበም፡፡	በሪፖርት ይገልጽ፡፡
8	ከዩኒቨርሲቲው የሰው ሃብት አስተዳደር እና ልማት ዳይሬክቶሬት በተሰጠው የለቀቁ አስተዳደር ሰራተኞች መግለጫ መሰረት ወ/ሮ አፍሪካ ደጀኔ በቀን 10/01/2011 ከተቋሙ መልቀቃቸው የተገለጸ ሲሆን ከመስከረም እስከ ሚያዚያ ደመወዝ እና 20% የበርሃ አበልን ጨምሮ በድምሩ ብር 30,115.20 የተከፈላቸው መሆኑ፤		X	ገንዘቡ ተመላሽ ለመደረጉ ማስረጃ አልቀረበም፡፡	በሪፖርት ይገልጽ፡፡
9	**በዋና ግቢ** ለተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ለተለያዩ አቅራቢዎች (ድርጅቶች) ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበውና ለተወራረደው ሂሳብ ብር **4,041,343.14** የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ፣		X	ተገቢ የክፍያ ደረሰኝ ለመቅረቡ ማስረጃ አልቀረበም፡፡	በሪፖርት ይገልጽ፡፡
	የ2010 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች				
10	በዩኒቨርሲቲው የሚመጡ እንግዳ መምህራን ከሚያገኙት ጥቅም ወይም ገቢ ላይ የገቢ ግብር መቀነስ ሲገባው ቅድመ ታክስ 2%(ሁለት በመቶ) በመቀነሱ በዋናው ግቢ ብር 197,407.64 እንዲሁም በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ብር 109,217.00 በድምሩ ብር 306,624.64 ልዩነት በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤		X	ገንዘቡ ለመሰብሰቡ ማስረጃ አልቀረበም፡፡	በሪፖርት ይገልጽ፡፡
11	በቀን 25/10/10 ዓ.ም በቁጥር DDU/LIS/00/117/2010 ከቤተ መፅሃፍትና መረጃ አገልግሎት ዳይሬክተር ለሰው ሃብት		X	ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ	በሪፖርት ይገልጽ፡፡

	ልማት እና ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት እንዲሁም በግልባጭ ለአካ/ም/ፕሬዚዳንት በተፃፈ ደብዳቤ በሲ.ኢ.ቢ.(CEB) ቤተ መፅሃፍት 5 የኮምፒዩተር RAM መጥፋታቸው የተገለጸ መሆኑ፣			ለመወሰዱ ማስረጃ አልቀረበም፡፡	
12	በቀን 02/02/10 ዓ.ም ከተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር ለአስተዳደርና ልማት ም/ፕሬዚዳንት እና ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በተፃፈ ደብዳቤ በተማሪዎች መኝታ ቤት በነሐሴ 2009 ዓ.ም እና በመስከረም 2010 ዓ.ም ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ዕረፍት መሄዳቸውን እና የክረምት ተማሪዎች ትምህረት መጨረሳቸውን ተከትሎ 225 ፍራሾች እና ሁለት 32 ኢንች ቴሌቪዥኖች መጥፋታቸው የተገለጸ መሆኑ፣		X	ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ ለመወሰዱ ማስረጃ አልቀረበም፡፡	በሪፖርት ይገልጽ፡፡
13	ከቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ እና ባለሙያዎች ጋር በጋራ የኦዲት ቡድኑ በንብረት አካላዊ እይታ ወቅት በተረዳው መሰረት ብሎክ ቁጥር 22 ባለ ሦስት ፌዝ ከ200 ሜትር በላይ የሚረዝም ኬብል ተቆርጦ መጥፋቱ የተገለጸ መሆኑ፤		X	ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ ለመወሰዱ ማስረጃ አልቀረበም፡፡	በሪፖርት ይገልጽ፡፡
14	ከምህንድስና ክፍል በቁጥር ድ/ዳ/ዩ/ምቡ/01013/2010 በቀን 26/2010 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ ማከሚያ ማዕከል የትልቅ SDB የብረት በሮች በቁጥር 45 ግምታዊ ዋጋ 41.58 ዶላር (41.58*27.68=1,150.93 *45=51,791.85) እንዲሁም የዊንግ ዶርሚተሪ 2 ህንጻ እድሳት ላይ እያሉ የተለያዩ የኤሌትሪክ ፊክስቸሮች (Breakers) ግምታዊ ዋጋ በድምሩ ብር 563,200.00 መጥፋታቸው የተገለጸ መሆኑ፣		X	ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ ለመወሰዱ ማስረጃ አልቀረበም፡፡	በሪፖርት ይገልጽ፡፡